# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ ተካትቶ ተግባራዊ መደረጉን እና በሥርዓተ ጾታ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ በመፍጠር ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር ........ 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀትና የሰው ሀይል ........ 3

የሚኒስቴር መ/ቤቱ  የፋይናንስ ምንጭ ........ 3

የኦዲቱ አላማ ........ 4

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ ........ 4

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና መመዘኛዎች (Audit issues and Evaluative criteria) . 4

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ........ 4

የሥራ ሂደት መግለጫ (Process descriptions) ........ 6

ክፍል ሁለት ........ 14

ግኝቶች ........ 14

የስርዓተ ፆታን ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣ በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተቱንና ተግባራዊነቱን በተመለከተ፣ ........ 14

በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ መፈጠሩንና ውጤታማነቱን ማረጋገጥን  በተመለከተ፣ ... 31

በስርዓተ ፆታ ጉዳይ ዙሪያ የተሟላ የመረጃ ፍሰት ስርዓት    መኖሩን ማረጋገጥን በተመለከተ፣ ........ 36

ክፍል ሦስት፡ ........ 39

መደምደሚያዎች ........ 39

ክፍል አራት፡ ........ 43

የማሻሻያ ሀሳቦች ........ 43

አባሪ 1 ........ 47

የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ ተካትቶ ተግባራዊ መደረጉን እና በሥርዓተ ጾታ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ በመፍጠር ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተካሄደ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. በአገራችን ካለው የሕዝብ ብዛት 50% ሴቶች፣ 30% የሚጠጋው ወጣት ሲሆን በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለስልጣን የ1999 ዓ.ም መረጃ መሰረት 55.5 እጅ የሚሆኑት ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት ናቸው፡፡ በመሆኑም ህዝብን በሚመለከት በአገሪቱ ውስጥ የሚካሄድ ማናቸውም እንቅስቃሴ እነኝህን የህብረተሰብ አካል ግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ እውነታ ሲታይ ህብረተሰባችን ለነዚህ አካላት ተገቢውን ትኩረት መስጠት እንዳለበት ያመለክታል፡፡
2. የሴቶች፣ ህጻናትና የወጣቶች እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት መብት ከአጠቃላይ በህብረተሰቡ ውስጥ ከሚካሄድ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ተለይቶ የሚታይ ባይሆንም፣ በዚህ የለውጥ ሂደት ውስጥ የተለየ ትኩረት ማግኘት የሚገባው ጉዳይ እንደሆነ አከራካሪ አይደለም፡፡
3. የሴቶች ጥያቄ የሰብዓዊ መብት ጥያቄ መሆኑን በመገንዘብ በአለም አቀፍ ደረጃ ኢትዬጵያ የተቀበለቻቸውን ስምምነቶች፣ ሴቶችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎችና ደንቦችን ለማስፈፀም በሽግግር መንግስቱ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የሴቶች ጉዳይ ንዑስ ዘርፍ በ1984 ዓ.ም እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ ይህ ንዑስ ዘርፍም በጥናት፣ በስልጠና፣ በውጭ ግንኙነት እና በማህበራዊ ጉዳዬች ላይ ትኩረት አድርጎ ይንቀሳቀስ ነበር፡፡
4. ከዚህም በተጨማሪ በሴቶች ላይ የሚታዩት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ መድሎዎች እንዲወገዱ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን የማስተባበር፣ የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት በማሳደግ የሴቶች ደህንነት እንዲጠበቅ የማድረግም ተልዕኮ ነበረው፡፡
5. የሕፃናትን ጉዳይ በተመለከተ የሚከታተል የሥራ ክፍል በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥር እስከ 1972 ዓ.ም ድረስ የነበረ ሲሆን፣ በ1972 ዓ.ም በሕፃናት ዙሪያ የሚደረጉትን እንቅስቃሴዎች የሚያስተባብር የሕጻናት ኮሚሽን ተቋቋመ፡፡ ኮሚሽኑም በሕፃናት መብትና ደህንነት ላይ ያተኮሩ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ከ

1983 የሽግግር መንግስት መቋቋም በኋላ በ1984 ዓ.ም የመዋቅር ለውጥ ተደርጎ የወጣቶችን ጉዳይ በማካተት የሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ድርጅት በመባል እስከ 1989 ዓ.ም ሲሰራ ከቆየ በኋላ፣ ከነሐሴ 1989 ዓ.ም ጀምሮ የሕፃናት፣ ወጣቶችና ቤተሰብ ጉዳይ መምሪያ ተብሎ ወደ ሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲጠቃለል ተደርገ፡፡

6. ስለሆነም መንግስት የሴቶችንና የሕፃናት ጉዳይ ልዩ ትኩረት እንደሚያስፈልገው በመረዳቱ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ሥር የነበረውን የሴቶች ጉዳይን እና በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥር የነበረውን የሕጻናት ክፍልን ተግባራትን በማዋሀድ በአዋጅ ቁጥር 471/98 የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲደራጅ ሲደረግ፣ የወጣቶች ጉዳይንም የሚከታተል በዚሁ አዋጅ የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ተቋቋመ፡፡
7. በመቀጠልም ለወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ከተሰጠው ሥልጣን ውስጥ የወጣቶችን ዘርፍ ከሴቶችና ሕጻናት ሚኒስቴር ጋር አንድ ላይ በማዋሀድ በአዋጅ ቁጥር 691/2003 የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በመባል እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

8. የሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጁ ቁጥር 691/2003 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡-
   - የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች መብትና ጥቅሞችን በማስከበር ዙሪያ ግንዛቤና ንቅናቄ እንዲፈጠር ያደርጋል፤
   - የሴቶች፣ የሕፃናትና የወጣቶችን ሁኔታ የሚያመለክቱ ዝርዝር መረጃዎች ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲታወቁ ያደርጋል፤
   - ሴቶችና፣ ወጣቶች በሀገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው ዕድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤
   - ሴቶችና ወጣቶች እንደፍላጎቶቻቸውና እንደ ችግሮቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እንዲችሉ ያበረታታል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
   - በፌዴራል መንግሥት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሴቶችንና ወጣቶችን ጉዳይ እንዲያካትቱ ስልት ይነድፋል፣ ይገመግማል፣ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፤
   - በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድልዎችን በጥናት በመለየት መድሎዎቹ የሚወገዱባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

- በሀገር አቀፍ ደረጃ የሴቶች ልዩ ድጋፍ መብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ስልት ይቀይሳል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- ሴቶች በተለያዩ የመንግስት አካላት በውሳኔ ሰጪ የሥራ ቦታዎች ለመመደብ በቂ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤
- የህፃናት መብትና ደህንነት እንዲጠበቅ የሚመለከታቸው አካላት ያስተባብራል፤
- ሴቶችንና ሕፃናትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ውሎችን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ለሚመለከታቸው አካላትም ሪፖርት ያቀርባል፡፡

የሚሉት ናቸው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀትና የሰው ሀይል

9. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመራው በአንድ ሚኒስትር እና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች ሲሆን በእነርሱም ስር 11 ዳይሬክቶሬቶች ይገኛሉ፡፡
10. የሚኒስቴር መ/ቤቱ በታህሳስ 13 ቀን በ2004 ዓ.ም ሴት 121 ወንድ 104 በድምሩ 225 ቋሚ ሰራተኞች ያሉትና በኮንትራት ደግሞ 6 ሴት እና 2 ወንድ በድምሩ 8 ሰራተኞች ነበሩት፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ  የፋይናንስ ምንጭ

- በ2000 በጀት ዓመት ለታቀዱ ስራዎች ማስፈፀሚያ መደበኛ በጀት ብር 4,889,400 የተፈቀደ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 4,077,296 ስራ ላይ ውሏል፡፡ በ2001 በጀት አመት መደበኛ በጀት ብር 6,494,500.00 የተመደበ ሲሆን፣ ለታቀዱ ስራዎች ማስፈፀሚያ ብር 5,900,000 ስራ ላይ ውሏል፡፡ በ2002 በጀት አመት  ለታቀዱ ስራዎች ማስፈፀሚያ ብር 11,325,600 ከተመደበው መደበኛ በጀት ብር 11,099,088.00 (98%) ስራ ላይ ውሏል፡፡ እንዲሁም ከልማት አጋሮች ብር 21 ሚሊዮን  ለማሰባሰብ ታቅዶ ብር 22.8 ሚሊዮን የተሰበሰበ ሲሆን፣ በዚህ በጀት የክልሎችን አቅም በስልጠናና በማቴሪያል በመደገፍ ስራ ላይ ከዋለው በጀት በተጨማሪ 4 ሚሊዮን ብር በቀጥታ ለክልሎች ተልኳል፡፡ በአጠቃላይ ከተሰበሰበው በጀት ብር 21,432,000.00 ወይም 94% ስራ ላይ ውሏል፡፡ በ2003 በጀት ዓመት ከመንግስት መደበኛ በጀት ብር 14,412,675.19 የተፈቀደ ሲሆን፣ ለታቀዱ ስራዎች ማስፈፀሚያ ብር 12,500,480.86 ወይም 87% ስራ ላይ ውሏል፡፡ከአጋር የልማት ድርጅቶች ለተለያዩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የማስፈፀሚያ ብር 30,599,475.84 ከተገኘው የበጀት ድጋፍ ብር 19,613,632.00 ወይም 64% ስራ ላይ ውሏል፡፡

## የኦዲቱ አላማ

11.የኦዲቱ ዓላማ ሴቶች በአገራችን በሚካሄደው ልማት ንቁ ተሳታፊና ከሚገኘው ኢኮኖሚያዊ እድገት እኩል ተጠቃሚነትን፣ የሴቶች ማህበራዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን፣ ሴቶችን ዝቅ አድርገው የሚመለከቱ አስተሳሰቦችንና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መወገዱን፣ የሴቶች የስራ ጫና መቃለሉን እና ሴቶች በየደረጃው እኩል ተሳታፊና የውሳኔ ሰጪነት ሚና እንዳላቸው በመገምገም የሚታዩ ድክመቶችን እና መንስዔዎቻቸውን በመለየት የማሻሻያ ሃሳብ ለማቅረብ ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ

12. ለኦዲቱ ከላይ በተጠቀሱት ዓላማዎች መሰረት ቁልፍ የኦዲት አካባቢው "ሴቶች በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ " የሚለዉ ተለይቷል፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና መመዘኛዎች (Audit issues and Evaluative criteria)

13. ከላይ የተመረጠውን የኦዲት ዓላማ ለማሳካት እና የተለየውን የኦዲት አካባቢ (audit area) ኦዲት ለማድረግ ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች የተመረጡ ሲሆን እነርሱም፡-

   1. የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣ በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተቱንና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ፣
   2. በሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ መፈጠሩንና ውጤታማነቱን ማረጋገጥ፣ እና
   3. በሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ዙሪያ የተሟላ የመረጃ ፍሰት ስርዓት መኖሩን ማረጋገጥ

የሚሉት ናቸው፡፡

14. በኦዲቱ ለተመረጡት እነዚህን ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ኦዲት ለማድረግ 52(ሀምሳ ሁለት) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

15.ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ነው፡፡ የዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ 2000 እስከ 2003 በጀት ዓመት ያለውን ጊዜ እና የ2004 በጀት


የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ድረስ ያለውን ጊዜ ነው። ዝርዝር ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ነው።

16. ለኦዲቱ የሚሆኑ መረጃዎች በናሙና በተመረጡ የፌዴራል አስፈጻሚ መ/ቤቶች፣ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የጅማ ዞን፣ የአጋሮ ከተማ እና የጎማ ወረዳ፣ በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የክልሉ የሴቶች፣ ሕጻናት ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ፣ የጋምቤላ ከተማ መስተዳደር እና የአበቦ ወረዳ የሴቶችና ሕጻናት ጽ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች እና የሚመለከታቸዉ የስራ ኃላፊዎችን በመጠየቅ እና መረጃዎችን በመገምገም መረጃ ተሰብስቧል፡፡
17. ከላይ እንደተመለከተው ኦዲቱን ለማድረግ ከተለያዩ መ/ቤቶች ማስረጃ መሰብሰቡ ተገልጿል፡፡ በዚህ መሰረት አንዳንድ በኦዲት ሪፖርቱ ውስጥ የተቀመጡ ግኝቶች፣ መደምደሚያዎችና የማሻሻያ ሃሳቦች በቀጥታ ሚኒስቴር መ/ቤቱን ብቻ የሚመለከቱ ሳይሆኑ፣ የተለያዩ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ ላይ የተሰማሩ የፌዴራል እና የክልል መንግስታዊ መ/ቤቶች እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን /አስፈጻሚ አካላትን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ለሁሉም መ/ቤቶች የሪፖርት ቅጂዎችን ለመላክ ከጊዜና ከአሰራር ግንኙነት አንጻር የተመቻቸ ባለመሆኑ፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ ከተጣለበት ኃላፊነት እና ከመ/ቤቶቹ ጋር ካለው የሥራ ግንኙነት ምክንያት ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት ሁሉ የሪፖርቱን መልዕክት እንዲያስተላልፍ እንጠይቃለን፡፡


## የሥራ ሂደት መግለጫ (Process descriptions)

### የሴቶችን ጉዳይ በሁሉም ዘርፎች እንዲካተት የማድረግ ዳይሬክቶሬት


### የማስፈፀሚያ ማዕቀፎች/ሰነዶች ዝግጅት የሥራ ፍሰት




## ጥናት የማካሄድ የስራ ፍሰት




# ስልጠና ግንዛቤ የመስጠት የሥራ ፍሰት




# ክትትል፣ ግምገማና ድጋፍ የማካሄድ የሥራ ፍሰት




# ግንዛቤ ለመፍጠር እና ንቅናቄ እንዲፈጠር ለማድረግ የሚረዳ ሰነድ የማዘጋጀት የስራ ሂደት ፍሰት




# በሴቶች ዙሪያ ግንዛቤ የመፍጠር የስራ ፍሰት



## በሴቶች ንቅናቄ ግንዛቤ ዙሪያ ቅንጅታዊ አሰራር የመፍጠር የስራ ፍሰት



## ክትትልና ግምገማ የማካሄድ የስራ ፍሰት



# ክፍል ሁለት

## ግኝቶች

### 2.1 የስርዓተ ፆታን ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣ በፐሮግራሞችና ፐሮጀክቶች መካተቱንና ተግባራዊነቱን በተመለከተ፣

**የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ እንዲካተት ለማድረግ የሚያግዝ የማስፈፀሚያ ሰነድን (Gender Mainstreaming Guide line) በተመለከተ፣**

18. የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ እንዲካተት ለማድረግ የሚያግዝ የማስፈፀሚያ ሰነድ (Gender Mainstreaming Guide line) ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ በተዘጋጀው የማፈጸሚያ ሰነድ ላይ ለሚመለከታቸው አካላት ሊተዋወቅና ሊሰራጭ ይገባል፡፡ የሰነዱ ተግባራዊነትና ያስገኙት ውጤትም ሊገመገም ይገባል፡፡

19. በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ የስርዓተ ፆታ ማካተቻ መመሪያ (National Gender Mainstreaming Guide line) በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሲሆን፣ በሰነዱ ላይ ከፌዴራል እና ከክልል ለተወጣጡ በሥርዓተ ፆታ ላይ ለሚሠሩ ሥልጠና መሰጠቱ ታውቋል፡፡

20. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል በኦሮምኛ ቋንቋ የማስፈጸሚያ ሰነዱ ያዘጋጀ፣ ለዞኖችና ወረዳዎች ሥልጠና መስጠቱ፣ በጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የሴቶች ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ ለአራት ሴክተር ቢሮዎች (ለጤና፣ ለትምህርት፣ ለግብርና እና ለፍትህ ቢሮዎች) የተባበሩት መንግስት የሥነ-ሕዝብ ድርጅት (UNFPA) የገንዘብ ድጋፍ የስርዓተ ፆታ ማካተቻ መመሪያ ተዘጋጅቶ የማስተዋወቅ ሥራ መሠራቱ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

21. ይሁን እንጂ የማስፈጸሚያ ሰነዱ የሚገኘው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባዘጋጀው ሥልጠና ላይ የተሳተፉ ግለሰቦች ጋር እንጂ ሰነዱ ለሴክተር መ/ቤቶች፣ ለክልሎች፣ ለዞኖችና ወረዳዎች ያልተላከ መሆኑን በናሙና በተመለከትናቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የዞንና የወረዳ መ/ቤቶች በቢሮዋቸውም ሰነዱ የማይገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡

22. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የተመረጡ የፌዴራል መ/ቤቶች ስለዚሁ ተጠይቀው በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀው የሥርዓተ ጻታ ማስፈጸሚያ ሰነድ እንዳልደረሳቸው፣ ነገር ግን የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ሴክተር ተኮር የሆነ የሥርዓተ ጾታ የማስፈጸሚያ ማንዋል (Sector specifc main streaming manual) ያዘጋጁና ስልጠናም ለሚመለከታቸው አካላት የሰጡ ሲሆን፣ የፌደራል ጥቃቅን

እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣንና የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበር ኮንፌዴሬሽን በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀው ሰነድ እንዳልደረሳቸው እና በራሳቸውም ያላዘጋጁ መሆኑ ታውቋል፡፡ የሰነዱን ተግባራዊነት በተመለከተ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በሥራቸው በሚገኙ መ/ቤቶች በየስራ ዘርፉ ለመካተቱ ክትትል የሚያደርጉ ሲሆን፣ በሌሎቹ የክትትል ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

23. ስለጉዳዩ ማስፈጸሚያ ሰነዱን ያላዘጋጁት መ/ቤቶች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ መ/ቤቱ የሥርዓተ ፆታ ማካተቻ መመሪያ (guideline) በማዘጋጀት ላይ እንደሚገኙ፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣንና የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበር ኮንፌዴሬሽን ሰነዱን ለዘርፋቸው በሚች መልኩ ያላዘጋጁበትን ምክንያት አልገለጹም፡፡ ክትትል የማያደርጉ መ/ቤቶች ደግሞ የግብርና ሚኒስቴር የማስፈጸሚያ ማንዋሉን ተግባራዊነት ላይ ክትትል ለማድረግ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ሲገልጹ፣ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ግን ለምን ክትትል እንደማያደርጉ ምላሽ አልሰጡም፡፡

24. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀው ሰነድ ከተዘጋጀ እድሜው አጭር ስለሆነ (የተዘጋጀው በ2003 ዓ/ም) ሰነዱን በማሳተም ለፌዴራልና ክልል ባለድርሻ አካላት የማስተዋወቂያ ሥልጠና እንደተሰጠ ገልጸዋል፡፡ በየደረጃው ያሉ ሁሉም ፈጻሚ አካላት በተደጋጋፊነት እንዲጠቀሙት በአማርኛ እየተተረጎመ መሆኑን ሀገራዊ የማስፈጸሚያ ሰነዱን ትግበራ ለማጠናቀር ለ14 የሴክተር መ/ቤቶች በያዝነው በጀት ዓመት (በ2004 ዓ.ም.) የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት ከሴክተራቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በሚጣጣም መልኩ የትግበራ ማንዋል እንዲያዘጋጁ እየተደረገ መሆኑንና በአብዛኛው መጠናቀቁን፣ በቀጣይም ከታዳጊ ክልሎች ጋር በተደረገ የዕቅድ ማስተካከያ በ2004 መመሪያውን ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ለማዘጋጀት የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ለመስጠት ስምምነት ላይ መደረሱን እና የቀሩት ፌዴራልና ክልል ሴክተሮች በራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ሰነዱን መሰረት በማድረግ የራሳቸውን ሰነድ አዘጋጅተው እንዲጠቀሙበት እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

25. የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ እንዲካተት ለማድረግ የሚያግዝ የማስፈፀሚያ ሰነድ በአገር አቀፍ ደረጃ ለሁሉም አስፈጻሚ አካላት አለመሰራጨቱና አስፈጻሚ አካላትም ለየዘርፋቸው በሚያመች መልክ ሰነዱን አለማዘጋጀታቸውና የስልጠና ሰነዱ ተሳታፊዎች ለተወከሉበት መ/ቤት አለመስጠታቸው ሠነዱን በፍጥነት ሥራ ላይ እንዳይውልና ተጠያቂነት እንዳይጠናከር አደርጎታል፡፡

## የሥርዓተ ፆታን ጉዳይ የሚከታተል አካል በመንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች መቋቋሙን በተመለከተ፣

26. የሥርዓተ ፆታን ጉዳይ በባለቤትነት የሚከታተል አካል በሁሉም የፌዴራል፣ በክልል፣ በዞን እና በወረዳ በሚገኙ የመንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሊቋቋም ይገባል፡፡ ለተቋቋሙት የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ የኃላፊነትና የተጠያቂነት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የሥርዓተ ፆታን ጉዳይ ለሚከታተል አካልና ሥርዓተ ፆታን በተመለከተ ለሚታቀዱ ስራዎች በጀት፣ ቢሮና ቁሳቁስ ሊሟላላቸው ይገባል፡፡

27. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከተመረጡ የፌዴራል መ/ቤቶች ውስጥ፣ በግብርና ሚኒስቴር፣ በውኃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ፣በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ እና በኢትዮጵያ የሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ጽ/ቤት መዋቅሩ በዳይሬክቶሬት ደረጃ ያለ መሆኑ፣ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ደግሞ በሰው ሀብት ዳይሬክቶሬት ሥር በቡድን ደረጃ መዋቀሩ፣ በፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ደግሞ በባለሙያ ደረጃ እንደተዋቀረ ታውቋል፡፡

28. በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን፤ በዞኑ ሥር ያሉ የሴክተር መ/ቤቶች ውስጥ የሥርዓተ ጾታን የሚከታተል አካል በአምስቱ መ/ቤቶች ብቻ በመዋቅር ደረጃ የተቋቋመ ሲሆን፣ በሌሎቹ ግን በተጠሪ (focal person) እንደተጨማሪ ሥራ የሚሠሩ መሆኑን፣ በጎማ ወረዳ ለ10 ሴክተር ጽ/ቤቶች መዋቅሩ ያላቸው ቢሆንም፣ ከግብርና ጽ/ቤት እና ትምህርት ጽ/ቤት በስተቀር ሌሎቹ መደበኛ ሥራቸው ሌላ በሆኑ ሠራተኞች በተጠሪ እንደተጨማሪ ሥራ እንደሚሠሩ፣ በአጋሮ ከተማ ደግሞ በሁሉም የሴክተር መ/ቤቶች የሥርዓተ ጾተ ጉዳይ የሚሠራው በተጠሪ መሆኑታውቋል፡፡

29. በጋምቤላ ህዝቦች ክልል፤ በክልሉ በሚገኙ ሁሉም ቢሮዎች የሴቶች ዩኒት መቋቋሙን፣ በጋምቤላ ከተማ መስተዳደር ካሉ 17 ጽ/ቤቶች ውስጥ በ8 በዩኒት ደረጃ መቋቋሙን በሌሎቹ ግን እንዳልተቋቋመ፣ በአበቦ ወረዳ በ6 የሴክተር ጽ/ቤቶች የሴቶች ዩኒትን የሚከታተሉ በሹመት መመደባቸውን እነሱን የሚያግዝ ባለሙያ ግን ያልተመደበላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

30. በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ፣ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን እና በጋምቤላ ክልል በአበቦ ወረዳ እና በጋምቤላ ከተማ መስተዳደር ሥር የመንግስት መ/ቤቶች በመዋቅር በግልጽ የሚታይ ቢሆንም፣ ሥራው በተጠሪ (focal person) እንደተደራቢ ሥራ እየሰሩ እንደሆነ፣ በቦታው ላይ ለተመደቡ ሰዎች ከሚመደብ

የደመወዝ በጀት ውጪ ለስራ ማስኬጃ የሚሆን (በሴቶች ዙሪያ ለሚሰሩ ስራዎች) በጀት የማይመደብ እና ቢሮና ቁሳቁስ የማይሟላ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

31. የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ለምን በተደራቢነት (focal person) እንደሚሰራ እና አስፈላጊው የሰው ኃይልና በጀት እንዳልተመደበ በናሙና የተመረጡ የፌዴራል መ/ቤቶች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በተደራቢነት መሠራቱ በቦታው ላይ ሰው ባለመቀጠሩ መሆኑን፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ዳይሬክተር ሲመልሱ፣ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በስተቀር በሁሉም የሴክተር ተጠሪ መ/ቤቶች የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን አስመልክቶ የተመደበ ባለሙያ የሌለ እና ከመደበኛ ስራቸው ላይ የሥርዓተ ጾታ ጉዳይን ደርበው የሚሰሩ ባለሙያዎች በመሆናቸው መደበኛ ሥራቸውን እንጂ ለሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ትኩረት እንደማይሰጡት ገልጸዋል፡፡

32. በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን የጎማ ወረዳ ሴቶች፣ ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት በወረዳው 39 ቀበሌዎች ያሉ ሲሆን፣ በቀበሌ ደረጃ የሴቶችና ሕጻናት መዋቅር ባለመኖሩ ሥራውን ለመሥራት አዳጋች እንደሆነባቸው አስታውቀዋል፡፡

33. ስለሁኔታው በናሙና የተመረጡት አስፈጻሚ አካላት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ሴቶችን በተመለከተ የሚታቀዱ ስራዎች በተወሠነ ደረጃ የበጀት፣ የሰው ኃይል እና የቢሮ ቁሳቁስ መኖሩን፣ የፕራይቬታይዜሽን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ እስካሁን በተደራቢነት እንደሚሠራ ቢሮም ሆነ ቁሳቁስ እንዳልተመደበ፣ የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበር ኮንፌዴሬሽን የሴቶች ጉዳይ መምሪያ በድርጅቱ ውስጥ እንዳሉት ሌሎች መምሪያዎች የተሟላ የቢሮ ቁሳቁስ፣ የመምሪያ ኃላፊ እና ባለሞያ ተመድቦለት በበጀትና በእቅድ እንደሚንቀሳቀስ፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሁሉም የሴክተር ተጠሪ መ/ቤቶች የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን አስመልክቶ በጀትን በተመለከተ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለስርዓተ ፆታ ተብሎ የሚመደብ በጀት ባይኖርም፣ መ/ቤቱ ግን ከአጋር ድርጅቶች ከሚገኝ ገንዘብ በተወሰነ መልኩ እንደሚንቀሳቀስ እና ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ቢሮና ቁሳቁስ የተሰጣቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

34. በጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት፤ በክልሉ በሚገኙ የሴክተር ቢሮዎች ውስጥ ሥርዓተ ጾታን ለሚመለከቱ ጉዳዮች በጀት ያልተመደበና የሰው ኃይልም ያልተሟላላቸው 30 ቢሮዎች መኖራቸው የክልሉ የሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡ በጋምቤላ ከተማ መስተዳደር በሚገኙ የሴክተር መ/ቤቶች የሥርዓተ ጾታን በሚመለከት የሰው ኃይል ችግር መኖሩ፣ ቢሮ የሌላቸውም እንዳሉ እና አንዳንዶቹ ቢሮ የተሰጣቸው እንኳን ቁሳቁስ እንደሌላቸው፣ ከሌሎች ከተማ መስተዳድር ጽ/ቤቶች አንጻር

ሲነጻጸር አነሰተኛ በጀት እንደሚመደብና ከደመወዝ ውጪ የስራ ማስኬጃ በጀት አለመኖሩን የከተማው የሴቶች ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡ በአበቦ ወረዳ የሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት የበጀት ችግር መኖሩ በየቀበሌው ኮሚቴ ለማቋቋም አዳጋች ሁኔታ የፈጠሩ እና ለህብረተሰቡ ወርዶ የግንዛቤ ስራ ለመሥራት አለማስቻሉን፣ በስድስቱ የሴክተር መ/ቤቶች በሹመት የተመደቡ እንጂ ሥራውን የሚያግዝ ባለሙያና በጀት ያልተመደበላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

35. በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን በሚገኙ የሴክተር መ/ቤቶች እንደ ጽ/ቤት ከሚበጀተው በጀት ውጪ የሥርዓተ ጾታ ጉዳይን ለሚከታተሉ ተጠሪዎች ተብሎ የሚበጀት በጀት አለመኖሩን የዞኑ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡ በአጋሮ ከተማ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ደግሞ በከተማው ባሉ የሴክተር ጽ/ቤቶች ሥርዓተ ጾታን አስመለክቶ ለሚታቀዱ ስራዎች በጀት ሙሉ በሙሉ ባይሆንም፣ የሚመደብ መሆኑን ነገር ግን ቢሮ፣ ቁሰቁስ እና የሰው ኃይል የተሟላ አለመሆኑን ገልጸዋል፤

36. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ በፌደራል ደረጃ በተደራቢነት (focal person) የሚሰሩት ተጠሪ መ/ቤቶች እንዳሉና አሁን ግን በመዋቅር አካተው መስራት የጀመሩ እንዳሉ በዚህ ዙሪያ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያዘጋጀው የምክክር መድረክ መረጃ በማሰባሰብና በመተንተን መዋቅሮችን ያሉበት ደረጃና የሰው ኃይል ይዘት፣ እንዲሁም የማኔጅመንት አባል የሆኑትንና ያልሆኑትንም የመለየትና በችግሮቹና በመፍትሔ ሃሣቦች ላይ በጋራ የመወያየት፣ እንዲሁም መ/ቤቶች የሥርዓተ ጾታ ጉዳይን ደርበው እንዳይሰሩ በመመካከርና በተገቢው ደጋፊ መረጃዎች በመደገፍ ቋሚ መዋቅር እንዲኖራቸው የማገዝ ሥራዎች ሚኒስቴር መ/ቤቱ እያከናወነ መሆኑን፣ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎችም በጋራ የማቀድና የመደገፍ ሥራ መጀመሩን ገልፀዋል፡፡

37. የሥርዓተ ፆታ ጉዳይን በሚመለከት ክፍል/መዋቅር ያልተቋቋመባቸው እና በተቋቋመባቸውም ባለሙያ ሳይመደብ እንደ ተደራቢ ሥራ መሰራቱ እና ለሚሰሩ ሥራዎች የስራ ማስኬጃ በጀት አለመመደቡ የኃላፊነትንና የተጠያቂነት አሰራር እንዳይኖር እና የሴቶችን ተጠቃሚነት በቅርበት ሆኖ ለመከታተል እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

<u>የስርዓተ ፆታን ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣ በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተቱን በተመለከተ፣</u>

37. የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣ በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ሊካተት ያስገኘውም ውጤት የሚገመገምበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

38. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት እንደተረዳነው፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥርዓተ ጾታ ጉዳዮች በፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተገቢው መልኩ መተንተናቸውንና በየስራው ዘርፍ መካተታቸውን የሚረጋገጥበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ለመደረጉ መረጃ አልቀረበም፡፡

39. በናሙና ከተመረጡ የፌደራል መ/ቤቶች በግብርና ሚኒስቴር፣ በውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበር ኮንፌዴሬሽን የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣ በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተቱና ተግባራዊነቱን ከዕቅድ እስከ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ የሚያከናውኑ ሲሆን የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፣ የፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲና ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የክትትልና የግምገማ ስርዓት የሌላቸው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

40. ስለጉዳዩ ክትትልና ግምገማ የማያደርጉ መ/ቤቶች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የስራ ክፍሉ አዲስ በመሆኑ አብዛኛውን የማደራጀት ስራ እየተሰራ እንደሆነና የተጠናከረ ስርዓት አለመዘርጋቱንና የስራ ክፍሉ ለወደፊቱ በሰው ኃይል ተሟልቶ ሲደራጅ የሚሠራ ጉዳይ መሆኑን፣ የፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ በፊት የስርዓተ ጾታ ጉዳይ እንዲካተት መደረጉ ክትትል ይደረግ የነበረ እና አሁን የተቋረጠ መሆኑን፣ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ መካተቱን ለማረጋገጥ የተዘረጋ የክትትል ሥርዓት የሌለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

41. ስለጉዳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ከፌዴራል የሴክተር መ/ቤቶች ጋር በተቋቋመው ፎረም በጋራ የተገመገመው ዓመታዊ ዕቅድ መሠረት በየሩብ አመቱ (quarterly) ሪፖርት የሚያቀርቡላቸው በመሆኑ ግብረ መልስ መስጠትና የጋራ ውይይት የሚደረግበት እንደሆነ፣ ሪፖርቱንም ሴክተር መ/ቤቶች የተጠሪ መ/ቤቶችንም ጨምረው እንዲያቀርቡ በፎረሙ ላይ ስምምነት ላይ የተደረሰ መሆኑን፣ ሴክተር መ/ቤቶችና ተጠሪ መ/ቤቶች የራሳቸውን ፎረም እንዲመሰርቱና በሴክተራቸው እየተናበቡ ሥራ እንዲሰሩ ስምምነት መደረሱንና ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኝ መሆኑ እና ሴክተር መ/ቤቶችና ተጠሪ መ/ቤቶች በየ6 ወሩ መገናኘት እንዳለባቸው በተሻሻለው የፎረሙ መተዳደሪያ ደንብ የተካተተ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የሚኒስቴር መ/ቤቱ በፎረም የሚገናኘው ከሴክተር መ/ቤቶች ጋር እንጂ

ለእነርሱ ተጠሪ ከሆኑ መ/ቤቶች ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት የሌለው መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

42. የስርአተ ጾታ ጉዳዮች በፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተገቢው መልኩ መተንተናቸውንና በየስራው ዘርፍ ባሉ ለየሴክተሩ ተጠሪ በሆኑ መሥሪያ ቤቶች መካተታቸው ያለመረጋገጡ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሰሩ ሥራዎች እና የተገኙ ለውጦችንም ለማወቅ፣ የሥርዓተ ፆታ ጉዳይ ተካቶ መተግበሩን ለማረጋገጥ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

<u>ሀገራችን በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ የገባችውን አለም አቀፍ ስምምነቶች/ ኮንቬንሽኖችን በተመለከተ፣</u>

43. ሀገራችን በስርዓተ ፆታ ጉዳይ ዙሪያ የገባችውን አለም አቀፍ ስምምነቶች/ ኮንቬንሽኖች ተለይተውና ተጠናቅረው ሊያዙ ይገባል፡፡ ስምምነቶቹም በየደረጃው የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ለሚመለከታቸው የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላት ሊተዋወቁና ሊሰራጩ ይገባል፡፡ ሥራ ላይ እንዲውሉ የሚደረግበትም ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ ተግባራዊነታቸውና ያስገኙት ውጤት በየዓመቱ ሊገመገም ይገባል፡፡

44. ሴቶችን አስመልክቶ የወጡና ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸው ኮንቬንሽኖች አፈጻጸም ያለበትን ደረጃ የሚያሳይ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተደራጅተው በሚኒሰቴር መ/ቤቱ ለመያዛቸው በኦዲቱ ወቅት መረጃው አልቀረበም፡፡

45. በናሙና ከተመረጡ የፌደራል መ/ቤቶች ጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበር ኮንፌዴሬሽን ስምምነቶቹ ተለይተው መያዛቸውን ሲገልጹ፣ የግብርና ሚኒስቴር፣ የፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት ኤጀንሲ፣ ኘራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን፤ በጋምቤላ ሕዝቦች ክልል፤ የክልሉ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ፣ የአበቦ ወረዳ የሴቶች፣ ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት የጋምቤላ ከተማ መስተዳድር የሴቶች፣ ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት፣ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን፤ የዞኑ የሴቶች ሕጻናት እና ወጣቶች ጽ/ቤት፣ የአጋሮ ከተማ የሴቶች፣ ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት እና በጎማ ወረዳ የሴቶች፣ ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ስምምነቶቹ የሌሉና ተለይተው ያልተያዙ መሆናቸውን እና በስምምነቶቹ ዙሪያ ስልጠና ያልተሰጣቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

46. አለምአቀፍ ስምምነቶችን በተመለከተ በናሙና የተመረጡት የፌዴራል መ/ቤቶቹ (የግብርና ሚኒስቴር፣ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ የጤና ጥበቃ ሚነስቴር፣ የፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት ኤጀንሲ፣ ኘራይቬታይዜሽንና የመንግስት

የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን) ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ አገሪቱ በሥርዓተ ጾታ ጉዳይ የገባቻቸው ስምምነቶች እንደማይደርሳቸው ነገር ግን የተወሰኑ አለምአቀፍ ስምምነቶች ከተለያየ ቦታ ለማግኘት ጥረት እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

47. በአለም አቀፍ ስምምነቶቹ ላይ ስልጠና ማግኘታቸውን በተመለከተ በናሙና የተመረጡ የፌዴራል አስፈጻሚ መ/ቤቶቹ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የግብርና ሚኒስቴር በስልጠና ወቅት እንደ ማጣቀሻ ብቻ እንደሚጠቀሙበት፣ የፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ በርዕሰ ጉዳይ ላይ በአለም አቀፍ የሴቶች ቀንን በማስመልከት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ለኤጀንሲው ኃላፊዎች የተከናወነ መሆኑን፣ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የተሰጠ ስልጠና የሌለ መሆኑን፣ የኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን የስራ ክፍሉ ለወደፊቱ በሰው ኃይል ተሟልቶ ሲደራጅ የሚሰራ ጉዳይ እንደሆነ፣ የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበር ኮንፌዴሬሽን አገራችን በሴቶች ዙሪያ የወጡ ሕጎች አለምአቀፍ የሠራተኞች ድርጅት (international labor organization, ILO) ስምምነት (convention) አስመልክቶ ለመሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር አመራሮች፣ ለፌዴሬሽን አመራሮች እና ለኢሠማኮ አመራሮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መሰጠቱን፣ የውኃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ኢትዮጵያ ሴቶችን አስመልክቶ የወጣውን ህግ እንደፈረመች ቢታወቅም አብዛኛውን እንዲያውቁ እንዳልተደረገ አንዳንድ በስራ አጋጣሚ ለማወቅ የቻልናቸው ኮንቬንሽኖች ለምሳሌ ቤጂንግ፣ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን በስራቸው ላሉ ተጠሪ መ/ቤቶች እንዲያውቁት እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡

48. በጋምቤላ ክልል፣ የክልሉ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት በስምምነቶቹ ዙሪያ ስልጠና ያልተሰጠ መሆኑ፣ የአበቦ ወረዳ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት በወረዳው የማስተዋወቅ ስራ ያልተሰራ መሆኑ ገልጸዋል፡፡፣ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን፣ የዞኑ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት በተለያየ ጊዜ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ እየተሰራ መሆኑን እንጂ በስምምነቶቹ ላይ ሥልጠና ያልተሰጠ መሆኑን፣ የአጋሮ ከተማ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት የተሰጠ ስልጠና ያለመኖሩን፣ የጎማ ወረዳ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ያሉት ስምምነቶች በእንግሊዘኛ ቋንቋ የቀረቡ በመሆናቸው በትክክል ሁሉም ለመረዳት እና በፅሁፍ ለውጦ ከታች ላሉት መዋቅሮች እና ለህብረተሰቡ ስልጠና ለመስጠትም ሆነ ለማሠራጨት የተቸገሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

49. ስለጉዳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሴቶችና ወጣቶች የማካተት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በቀረበ መጠይቅ በተሰጠ ምላሽ፣ አለም አቀፍ ኮንቬንሽኖቹ/ ስምምነቶቹ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተለይተው መያዛቸውን፣ በተለያዩ ጊዜም ወቅቱን የጠበቀ ሀገራዊ ሪፖርት በአለም አቀፍ ደረጃ የቀረበ መሆኑን፣ ተግባራዊነቱን በተመለከተ በትክክልም እየተተገበረ እንደሆነ፣ ኮንቬንሽኖቹ/ስምምነቶቹ በተለያየ መልክና በተለያዩ አስፈጻሚ አካላት ስለሚፈጸም ለብቻው የሚታይበት ሁኔታ የጐላ እንዳልሆነ፣ ሌሎች ዕቅዶችና ፕሮግራሞች አፈፃፀም ሲታይ ይህም አብሮ የሚታይ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ስምምነቶቹን የመያዝ፣ የመተርጎምና የማስተዋወቅ ሥራን በአዋጅ ኃላፊነት የተሰጠው ለሰብአዊ መብት ኮሚሽን መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን መልስ ይስጡ እንጂ፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ መረጃዎቹ ተጠናቅረው ለመያዛቸው መረጃ ያልቀረበ በመሆኑና በአዋጅ ለሚኒስቴር መ/ቤቱም በግልጽ ኃላፊነቱ የተሰጠው በመሆኑ የተሰጠውን መልስ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

50. በስምምነቶቹ ላይ ሥልጠናን በቂ ዝግጅት የተደረገበትና በተለያዩ ባለሙያዎች በቅርቡ በህዳር 13-16 2004 ዓ.ም. በሀዋሳ ከተማ የፌዴራልና የክልል ሴቶች ጉዳይ መዋቅሮች ኃላፊዎች የተሳተፉበት ስልጠና መሰጠቱን፣ በስልጠናው ከተገኘ ግብረ-መልስ (Feed back) ከዚህ በፊት በዚህ ዙሪያ ጥልቅ እውቀት እንዳልነበረ የተገለጸበት ሁኔታ የነበረ መሆኑን፣ ስለኮንቬንሽኖች ተግባራዊነት በየጊዜው የሚዘጋጁ ሀገራዊ ሪፖርቶች ዝግጅት ሂደት ስለአፈፃፀሙ መገምገሚያ የሚጠቀሙበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

51. ስለጉዳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሴቶችና ወጣቶች ንቅናቄ ተሳትፎ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በቀረበ መጠይቅ በተሰጠ ምላሽ፣ ተለይተው (booked) ሆነው እንደሌሉ፣ ነገርግን በሶፍት ኮፒ በቢሮዋቸው እንደሚገኝ፣ በመ/ቤት ደረጃ የመረጃ አያያዝ ችግር በከፍተኛ ደረጃ መኖሩ፣ ስምምነቶቹን ስራ ላይ ለማዋል የተሰራን ስራ በተመለከተ በክፍሉ ብዙም ይህንን አስመልክቶ የሚሰራ ሥራ የሌለ መሆኑ ይህ የማካተት (mainstreaming) ሥራ እንደሆነ፣ ነገር ግን በዚህ አመት ሁለት ጊዜ የተወሰኑ ነጥቦችን ወስደው የማስተዋወቅ ሥራ መሰራቱ፣ ግምገማን በተመለከተ አንደኛው በየስድስት ወሩ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በእቅድ አፈጻጸም ዙሪያና የተገኘውን ውጤት አስመልክቶ ክልሎች፣ ማህበራት፣ ከሃያዎቹ (20) የፌደራል ሴክተር መ/ቤቶች እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለሙያዎች በተገኙበት የሚካሄድ መሆኑ ሁለተኛው የመስክ እይታ የግምገማ ሥርዓት ያለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

52. ሥርዓተ ፆታን አስመልክቶ አገራችን የገባቻቸው አለም አቀፍ ኮንቬንሽኖቹ/ስምምነቶቹ የፌዴራሉ የስራ ቋንቋ ወደሆነው አማርኛ እና ወደ የክልሉ የስራ ቋንቋ አለመተርጎማቸው

በየደረጃው ከፌዴራል እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ ላሉ አስፈጻሚ አካላት እና ለህብረተሰቡ ማሠራጨትም ሆነ ግንዛቤ ለመፍጠር እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

<u>በሴቶች ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶችን በተመለከተ፣</u>

53. ከሴቶች ጋር በተያያዘ በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ያለውን አመለካከትና ልምድ አስመልክቶ ጥናት ሊደረግ ይገባል፡፡ በተለይም በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎችና ኋላ ቀር አስተሳሰቦች በጥናት ሊለዩ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የፌዴራል፣ የክልል መ/ቤቶች፣ የስርዓተ ፆታ ጉዳይ ቢሮዎችና /ጽ/ቤቶች የአቅም ክፍትት ጥናት ሊካሄድ ይገባል፡፡ በጥናት የተለዩት መድልዎች የሚወገዱባቸውን የመፍትሔ ሀሳቦች በማቅረብ ተግባራዊ ሊደረጉና ያስገኘው ለውጥ በየጊዜው ሊገመገም ይገባል፡፡

54. በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተወሰኑ የተጠኑ ጥናቶች መኖራቸውን፣ ነገር ግን በጥናቱ መሰረት እርምጃ የተወሰደ ስለመሆኑ መረጃ አልቀረበም፡፡ ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው  አሁን በሥራ ላይ የዋሉት ፖሊሲዎችና ፓኬጆች ሲዘጋጁ በመጀመሪያ በተካሄዱ ጥናቶችን መሰረት በማድረግ የተቀረጹ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

55. በናሙና ከተመረጡ የፌደራል መ/ቤቶች ውስጥ በውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጥናቶች መጠናታቸውን፣ በግብርና ሚኒስቴር የዳሰሳ ጥናቶች የተካሄዱ መሆናቸው፣ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በመ/ቤቱ የሚገኙ ሴቶችን የትምህርት ደረጃ ለማወቅ የሚያስችል የደሰሳ ጥናት የተከናወነ መሆኑን፣ በፌደራል የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርኘራይዞች ልማት ኤጀንሲ የኤጀንሲው ሴት ሠራተኞች አቅምን ለማጎልበትና ድጋፍ ለመስጠት በሚል ያሉባቸውን ችግሮች እንዲሠጣቸው የሚፈልጓቸው ድጋፎች ለመለየት የሚያስችል ጥናት የተካሄደ ቢሆንም፣ ውጤቱ ውሳኔ ሳይሠጥበት የቀረ መሆኑን፣ በጥቃቅን እና አነስተኛ ልማት ዘርፍ የሚገኙ ሴት ኢንተርኘሪነሮች ችግር በመለየት የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ የሚያስችል የ5 ዓመት ኘሮጀክት ተቀርፆ ለውጪ ጉዳይ ሚኒስቴርና ለሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር የቀረበ ቢሆንም፣ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈንድ ባለመለቀቁ ኘሮጀክቱ እስካሁን ተግባራዊ ሳይሆን የቀረ መሆኑን፣ ኘራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ሠራተኛ ማህበር ኮንፌዴሬሽን የተጠኑ ጥናቶች ያለመኖራቸው ታውቋል፡፡

56. የኦሮሚያ ክልል የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ በ2003 በናሙና በተመረጡ ዞኖችና ወረዳዎች በክልሉ በሚገኙ ሴቶች ላይ ስለሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በተመለከተ የደሰሳ ጥናት ለማከናወን ለተመረጡት ዞኖችና ወረዳዎች፣ መጠይቅ የላከ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

57. ስለጉዳዩ ክልሎቹ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን የዞኑ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤት በክልሉ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤት ከህግ አካላት፣ በዞኑ ውስጥ ከሚገኙ ከወረዳ ሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤቶችና ከማህበረሠቡ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ዙሪያ የተላከ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ለክልሉ ቢሮ ከመላኩ በፊት ቀሪ ቅጅ በማስቀረት መረጃው ያላቸው ቢሆንም፣ መረጃዎቹ በጽ/ቤታቸው በኩል ያልተተነተኑ መሆኑን፣ የጎማ ወረዳ የሴቶችና ህጻናት ጽ/ቤት የተጠና ጥናት ያለመኖሩን ነገር ግን በ2004 በዕቅድ መያዙን፤ የአጋሮ ከተማ የሴቶች ሕጻናት እና ወጣቶች ጽ/ቤት ጥናት ያላጠኑ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

58. በጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የክልሉ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤት በሴቶችና በህፃናት ላይ የሚፈፀሙ የኃይል ጥቃቶች ዙሪያ በተባበሩት መንግስታት የሥነ ሕዝብ ድርጅት (UNFPA) የገንዘብ ድጋፍ ጥናት የተካሄደና ጎጂ ልማዳዊ የኃይል ጥቃቶች የተለዩ መሆናቸውን፤ የጋምቤላ ከተማ መስተዳደር የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤት በከተማ ውስጥ ያሉትን ስራ አጥ ሴቶች በተመለከተ ብዛታቸው እና የትምህርት ደረጃቸውን ዝርዝር ከ5 ቀበሌዎች ደብዳቤ ልከው ተሞልቶ መመለሱን ነገር ግን በጀት የሚጠይቁ ጥናቶችን በተመለከተ የሚመደብ በጀት ባለመኖሩ እንዳልተከናወነ፤ የአበቦ ወረዳ ሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤት የተጠና ጥናት አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

59. በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሟላ ጥናት አለመከናወኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተከናወኑት ጥናቶችም ለአስፈጻሚ አካላት እንዲደርሱ አለመደረጉ በሥርዓተ ፆታ ዙሪያ ያለውን ክፍተት ለይቶ የመፍትሔ እርምጃ ለመውሰድ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

__በሥርዓተ ጾታ ዙሪያ በሚሰሩ አስፈጻሚ አካላት መካከል ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በተመለከተ፤__

60. የስርዓተ ፆታን ጉዳይ አስመልክቶ በተለያዩ አካላት የሚከናወኑ ፕግራሞች ተደራራቢ እንዳይሆኑ በቅንጅት የሚታቀድበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

61. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩት በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር እና በግብርና ሚኒስቴር ለየሚኒስቴር መ/ቤቶቻቸው ተጠሪ ከሆኑ መ/ቤቶች ጋር ሥርዓተ ጾታን በተመለከተ በጋራ የሚያቅዱ ሲሆን፤ የጋምቤላ እና የኦሮሚያ ክልሎች ዞኖችና ወረዳዎች የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ (ጽ/ቤት) ጋር ስምምነት ለመፈራረም ሲንቀሳቀሱ የክልሎችንም ሆነ የዞንና የወረዳ የሴት ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች ግን እንዲያውቁት እንደማይደረግ ታውቋል፡፡

62. ስለጉዳዩ ክልሎች ዞኖችና ወረዳዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በጋምቤላ ክልል የአበቦ ወረዳ የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ጽ/ቤት በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ የሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በወረዳው የሚንቀሳቀሱ የሌሉ መሆናቸውን፤ የጋምቤላ ከተማ መስተዳደር የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ጽ/ቤት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፕሮግራማቸውን የሚያሳውቁትም ሆነ እውቅና የሚያገኙት በክልሉ እንደሆነ እነሱ የሚያውቁት ነገር ያለመኖሩ፣ ከአንድ  Brothers and sisters ከሚባል መንግሥታዊ ካልሆነ ድርጅት ጋር ግን እየሠሩ እንደሚገኙ፤ በጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ጽ/ቤት በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ የሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚንቀሳቀሱ የሌሉ መሆናቸውን፣ ነገር ግን ሲኖር በጋራ እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡

63. በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን የዞኑ ሴቶች ሕጻናት እና ወጣቶች ጽ/ቤት በዞኑ ካሉት የሴቶች ፌዴሬሽን፣ የሴቶች ማህበር እና የሴቶች ሊግ ጋር በጋራ የሚያቅዱበት ሁኔታ መኖሩን፣ በጎማ ወረዳ የሴቶች ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት በወረዳው ካለ አስፈጻሚ አካላት ጋራ በቅንጅት የሚያቅዱበት ሁኔታ ያለ ሲሆን ሥራዎችን ግን በጋራ የመገምገም ልምድ እንደሌለ፣ የአጋሮ ከተማ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ደግሞ መንግስታዊ ከሆኑና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

64. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው፣ በመጀመሪያ ደረጃ ሁሉም አስፈጻሚ አካላት የስርዓተ ጾታን ጉዳይ አስመልክቶ በፖሊሲዎቹ፣ በፕሮግራሞቹ/ ፕሮጀክቶች፣ በእቅዶቻቸው ወዘተ አካተው እንዲተገብሩ በወል ስልጣን በአዋጅ የተሰጠ መሆኑ፣ አስፈጻሚ አካላት ይህንን ለመፈጸማቸውና የሚፈለገው ውጤት መምጣቱን የመከታተል፣ የመደገፍና የአሰራር ስርዓትን የመዘርጋት ስራ ደግሞ ለሚ/ር መ/ቤታቸው የተሰጠ ኃላፊነት በመሆኑ ዕቅድን በጋራ የማቀድ፣ በጋራ አፈጻጸሙን የመከታተልና የመገምገም ስራዎች በመሰራት ላይ መሆናቸውን ለዚህም የጋራ ፎረም ተቋቁሞ በመሰራት ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

65. በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ የተለያዩ አካላት በቅንጅት አለመሰራታቸው፣ የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በህጎች ፖሊሲዎችና መርሀግብሮች አፈፃፀም፣ በአቅም ግንባታና በመረጃ ልውውጥ ዙሪያ ያለውን ግንኙነት ደካማ ከማድረጉም በላይ ያለውን ውስን ሀብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዳይውል ያደርጋል፡፡

## ከስርዓተ ፆታ ጋር በተያያዘ በተለያየ መልክ የሚገኙ ፈንዶችን በተመለከተ፣

66. ከስርዓተ ፆታ ጋር በተያያዘ በተለያየ መልክ የሚገኙ ፈንዶች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተመዝግበው ሊያዙ ይገባል፡፡ፈንዶቹም ለታቀደላቸው ተግባር መዋላቸውን የሚረጋገጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

67. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በጋምቤላ ክልል ከዚህ ቀደም በሴቶች ልማት ፈንድ አማካኝነት የገንዘብ ድጋፍ በማግኘት በጋምቤላ ከተማ ለተቋቋሙ 10 የሴቶች ማህበራት ብር 307,349.50 (ሦስት መቶ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ አርባ ዘጠኝ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ወስደው ሥራ የጀመሩ ቢኖሩም በአሁን ሰዓት ግን ስራ ላይ የሚገኘው አንድ ማህበር ብቻ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

68. በሴቶች ልማት ፈንድ አማካኝነት የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸው የተለያዩ አካላት የልማት ፈንዱ ሥልጣንና ኃላፊነት ወደ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተላለፈ በኃላ አሁን እነዚህ ፈንድ የወሰዱ የተለያዩ አካላት ያሉበትን የፋይናንስ ሆነ ፈንዱን ለወሰዱበት ዓላማ ተግባራዊ ማድረጋቸውን ለማወቅ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የተዘረጋው ሥርዓትና የተያዘው መረጃ ለኦዲቱ አልቀረበም፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በተለያየ መልክ የሚገኙ ፈንዶች ምንጫቸውና ለምን ዓላማ እንደተገኙ የጊዜ ገደባቸውን ጨምሮ በሚገልጽ መንገድ ተለይተው ለመመዝገባቸውና ለመያዛቸው፣ ፈንዶቹ ለታለመላቸው ዓላማና ተግባር መዋላቸው በክትትል የሚረጋገጥበት እና የሚገመገምበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉም መረጃው አልቀረበም፡፡

69. ስለሁኔታው የጋምቤላ ከተማ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ተጠይቀው በጋምቤላ ከተማ ከዚህ በፊት ከሴቶች ልማት ፈንድ እገዛ የተደራጁ ማህበራት ስራ ሲያቆሙ የባንክ ደብተራቸው እስከ አሁን የሚገኘው በክልሉ ቢሮ ሲሆን፣ መልሰው ወደ ስራ እንዲገቡ ለማድረግ ሲሞከር መጀመሪያ ገንዘባቸው እንዲለቀቅ ጥያቄ ቢያቀርቡም አፋጣኝ ምላሽ ከክልሉ ቢሮ ባለማግኘታቸው መልሶ ማደራጀት እንዳልቻሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡

70. ስለጉዳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለእስትራቴጂያዊ ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በቀረበ መጠይቅ በተሰጠ ምላሽ፣ በአጠቃላይ የሴቶች ልማት እንቅስቃሴ ፕሮጀክትን በተመለከተ ፕሮጀክቱ ሲካሄድ የነበረው በየክልሎች ስለነበር ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የፕሮጀክቱን ስራ የተረከቡት ክልሎች መሆናቸው፣ ፕሮጀክቱ ለሴቶች ገቢ ማስገኛ ስራዎች የሰጣቸው መነሻ ካፒታል ተንከባላይ ካፒታል (Revolving Fund) ሳይሆን ስጦታ (Grant) በሚል አስተሳሰብ ጋምቤላ ክልል ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ክልሎች በተመሳሳይ

ሁኔታ ተደራጅተው የነበሩ ማህበራት አንዳንድ ቦታ ገንዘቡን ተከፋፍለው እንደተበተኑ፣ አንዳንዶች ደግሞ ገንዘብና ንብረት ሳይከፋፈሉ የተበታተኑ መሆኑ ሌሎች ደግሞ በጋራ እየሰሩ ውጤታማ እንደሆኑ በተለያዩ ጊዜያት ከክልሎች ጋር በተደረጉ የጋራ መድረኮች መረዳት የተቻለ መሆኑ፣ ነገር ግን ከገንዘብ ጋር ተያይዞ የእያንዳንዱ ማህበራት መረጃ ያለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

71. የስርዓተ ጾታ ጉዳይን ለማስፈጸም የሚረዳ በጀት ከመንግስትና ከሚመለከታቸው አጋር ድርጅቶች (UN agencies) የሚገኝ መሆኑን የመንግስት በጀት ባለው የሀገሪቱ የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የሚፈጸም እንደሆነ ከአጋር ድርጅቶችም የሚገኝ በጀት ድርጅቶቹና መንግሰት በጀቱን ስራ ላይ ለማዋል በተስማሙበት ስምምነት መሰረት ስራ ላይ እንደሚውል፣ ድርጅቶቹም ስራ ላይ መዋሉን ሪፖርት በሚደረግላቸውና በሚካሄድ የጋራ መድረክ የሚያረጋግጡበት አሰራር መኖሩን ለምሳሌ በተጨባጭ የስርዓተ ጾታ ጉዳይን ለማስፈጸም ከተለያዩ  አጋር ድርጅቶች (Multi laterals & Bi-laterals) የሚገኝን በጀት ወደ አንድ ቋት Gender Pool Fund በሚል ስያሜ  በማስገባት እስካሁን ድረስ ስራ ላይ መዋሉን፣ በሌላ በኩል የስርዓተ ጾታ ጉዳይን አንዱና ዋና ያደረገ የመንግስትና የአጋር ድርጅቶች የጋራ ፕሮግራም (Joint Program) በመንደፍ ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝና እነዚህም በጀቱም ሆነ የፊዚካል ስራዎቹ በጋራ ክትትልና ግምገማ የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በሴቶች ልማት ፈንድ ይተዳደር የነበርውን ፈንድና ሥራ በተመለከተ ገና ርክክቡ ያላለቀ እና የትኛው ኃላፊነት ለማን ይስጥ የሚለው ውሳኔ ገና ተሰጥቶ ባለማለቁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

72. ከሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በተለያየ መልክ የሚገኙ ፈንዶች ምንጫቸውና ለምን ዓላማ እንደተገኙ የጊዜ ገደባቸውን ጨምሮ በሚገልጽ መንገድ ተለይተው አለመመዝገባቸው፣ ፈንዶቹ ለታለመላቸው ዓላማና ተግባር መዋላቸው የሚረጋገጥበት እና የሚገመገምበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ የተገኙት ፈንዶች የጊዜ ገደባቸው ሳያልቅ ለታለመላቸው ዓላማ ስለመዋላቸው ማረጋገጥን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪ መረጃውን ለሚፈልግ አካል በቀላሉ እንዳይገኝ ያደርጋል፡፡

<u>ሴቶች በእኩልነት ላይ በተመሰረተ የደረጃ እድገት፣ ዝውውር፣ የኮሚቴ አወቃቀር፣ ስንብትና ስልጠና የማግኘትና ተጠቃሚ መሆንን በተመለከተ፣</u>

73. ሴቶች በእኩልነት ላይ በተመሰረተ የደረጃ እድገት፣ ዝውውር፣ የኮሚቴ አወቃቀር፣ ስንብትና ስልጠና የማግኘትና ተጠቃሚ የመሆን መብታቸው መጠበቁን ክትትል የሚደረግበት ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

74. በጋምቤላ ክልል የአበቦ ወረዳው የደረጀ እድገት፣ የዝውውር፣ የኮሚቴ አወቃቀር፣ ስንብትና ስልጠናን የሚመለከት ኮሚቴ ቢቋቋምም ለሴቶች ተብሎ ተለይቶ የመጣውን ሴቶች የሚሳተፉበት ለወንዶችና ለሴቶች የመጣውን እኩል በእኩል በሆነ መልኩ በዕጣ የሚለይ በመሆኑ ቅድሚያ ለሴቷ የሚሰጥበት ሁኔታ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

75. ቀደም ሲል የደረጃ እድገት ዝውውር እና ቅጥርን በሚመለከት የስርዓተ ፆታ ክፍል ቀጥተኛ ተሳታፊ የነበረ ሲሆን በ2000 ዓ.ም. በሲቪል ሰርቪስ በወጣ መመሪያ መሠረት የኮሚቴ አሠራር በመቅረቱ በየጊዜው የሚካሄደውን ሁኔታ እንደቀድሞ የሴቶችን ተጠቃሚነት ባገናዘበ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ለመፈተሽ የማይቻል መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

76. ስለጉዳዩ የፌደራል መ/ቤቶች፣ ክልሎች ዞኖችና ወረዳዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በየስራ ክፍሎች በተወሰነ ደረጃ በግንባር በመቅረብ ውይይት የሚደረግ ቢሆንም የተጠናከረ ስራ ያለመሰራቱን፤ የፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ በፊት ይከናወን የነበረ ሲሆን፣ አሁን ግን የማይሰራ መሆኑን፣ በፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ያለመኖሩን፣ የውኃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ቀደም ሲል የደረጃ እድገት ዝውውር እና ቅጥርን በሚመለከት ክፍላቸው ቀጥተኛ ተሳታፊ የነበረ መሆኑን ሆኖም በ2002 ዓ.ም በሲቪል ሰርቪስ በወጣ መመሪያ መሠረት የኮሚቴ አሠራር በመቅረቱ በየጊዜው የሚካሄደውን ሁኔታ እንደቀድሞ ለመፈተሽ ያልቻሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

77. በጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የክልሉ የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ ደግሞ በየቢሮ የሚገኙ የሴቶች ዩኒቶች እንደሚከታተሉና ሆኖም ስልጠና የማግኘት እና ተጠቃሚ የመሆን መብታቸው ረገድ ግን አሁንም ሴቶችን አሳንሶ የማየትና ያለማሳተፍ ችግር እንዳለ፣ የአበቦ ወረዳ የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ጽ/ቤት በወረዳ ደረጀ እድገት፣ ዝውውር፣ የኮሚቴ አወቃቀር፣ ስንብትና ስልጠናን የሚመለከት ኮሚቴ የተቋቋመ ቢሆንም፣ ለሴቶች የመጣውን ሴቶች የሚሳተፉበትን ለወንዶችና ለሴቶች የመጣውን እኩል በእኩል በሆነ መልኩ በዕጣ የሚለይበት ሁኔታ በመኖሩ ቅድሚያ ለሴቷ የሚሰጥበት ሁኔታ የሌለ መሆኑን፤ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የጐማ ወረዳ የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ጽ/ቤት እነዚህ ጉዳዮች በተመለከተ በቢሮዋቸው አንድ ተወካይ በቦታው በመገኘት ነገሮችን የሚከታተልና የሚያስፈፅም ቢሆንም የሚፈለገውን ውጤት አስገኝቷል ማለት ግን እንደማይቻል ገልጸዋል፡፡

78. በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የጅማ ዞን የዞኑ የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ጽ/ቤት እንደኮሚቴ ከተለያዩ መ/ቤቶች ጋር በመሆን ሴቶች እንዳይበደሉ የሚሠራ ስራ መኖሩን ሆኖም ግን አሁንም በሁሉም መ/ቤቶች እየተተገበረ እንዳልሆነ፤ የአጋሮ ከተማ የሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤት ይህን በተመለከተ በነዚህ ጉዳዮች ላይ በሁሉም ቦታ ባይሆንም የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ተወካይ በሚገኝበት አንዳንድ ቦታ ላይ ክንውን እንደሚደረግ አልፎ አልፎም በቅንጅት እየሠሩ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

79. ስለጉዳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሴቶችና ወጣቶች የማካተት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በቀረበ መጠይቅ በተሰጠ ምላሽ፣ ይህንን በተመለከተ በፎረም ላይ መወያየታቸውን፣ ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ጋር በመሆን ዳሰሳ ለማከናወን መጠይቅ ተዘጋጅቶ ከፎረሙ አባላት መረጃ የተሰበሰበ መሆኑንና በሚታዩ ክፍተቶች መሠረት በቀጣይ የመፍትሔ እርምጃ የሚወሰድበት እንደሚሆን ገልፀዋል፡፡

80. ሴቶች በእኩልነት ላይ በተመሰረተ የደረጃ እድገት፣ ዝውውር፣ የኮሚቴ አወቃቀር፣ ስንብትና ስልጠና የማግኘትና ተጠቃሚ የመሆን መብታቸው መጠበቁን ለማረጋገጥ የክትትል ስርዓቱ የላላ መሆን፣ የሴት ሰራተኞችን መብት ለማስከበር የሚደረገውን ሂደት አዳጋች ያደርገዋል፡፡

<u>በሰው ሰራሽ ፣ በተፈጥሮ አደጋዎች እና በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለተጎዱ ሴቶች ድጋፍና እንክብካቤ ማግኘታቸውን በተመለከተ፣</u>

81. በሰው ሰራሽም፣ በተፈጥሮ አደጋዎች እና በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለተጎዱ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሴቶች ትኩረት የሚያገኙበት፣ የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት የሚያገኙበት ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡ በደል ለደረሰባቸው ሴቶች የምክርና የሙያ አገልግሎት የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የሚዘረጋውም ሥርዓት የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ ሊሆን ይገባል፡፡

82. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ ክልሎች፣ዞኖች/ከተሞችና ወረዳዎች በተፈጥሮ አደጋ ዙሪያ የሚሠሩ ሥራዎች ከአደጋ መከላከል ጽ/ቤት ጋር በቅንጅት የሚሰራ ቢሆንም፣ በሚፈለገው ደረጃ ሴቶችን ተጠቃሚ ያላደረጉ፣ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን የጎማ ወረዳ የተፈጥሮ አደጋ የመከላከል ሥራ በጋራ ለመሥራት ፍቃደኛ ያልሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መኖራቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

83. በተፈጥሮ አደጋዎችም ሆነ በሰው ሰራሽ/በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚጠቁ ሴቶች ድጋፍና እንክብካቤ የሚያገኙበት ስርዓት በየደረጃው ተዘርግቶ ተግባራዊ ለመደረጉ መረጃ አልቀረበም፡፡

84. ስለጉዳዩ በናሙና የታዩት አስፈጻሚ አካላት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የክልሉ የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ምግብ ዋስትና ቢሮ የመ/ቤቶች የሴቶች ዩኒቶች በኩል ክትትል እየተደረገ ሪፖርት የሚደርሳቸው ቢሆንም፣ ተጠሪዎቹን አደጋ በተከሠተበት ጊዜ ወደ መስክ በመሄድ ስንት ሴቶች ለአደጋ እንደተጋለጡ ለማየት እድል የማይሰጣት መሆኑ፣ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ተጎጂ ለሆኑ ሴቶች በቤተሠብ ህጉ መሠረት የህግ ድጋፍ የሚደረግ መሆኑን፣ የአበቦ ወረዳ የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ጽ/ቤት የተፈጥሮ አደጋዎች ሲደርሱ አደጋ መከላከያና ዝግጁነት ጋር በቅንጅት የሚሰሩ መሆኑን፣ ለሠው ሠራሽ ችግሮች (ድብደባ፣ አስገድዶ፣ መድፈር ...ወዘተ/ ሲያጋጥም ወንጀለኞችን ወደ ህግ ተጎጂዎችንም ደግሞ ወደ ህክምና እንዲሄዱ የሚያደርጉ መሆኑን፣ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ዙሪያ የሚሠሩ የጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አስወጋጅ ኮሚቴ ለጽ/ቤታቸው ተጠሪ የሆኑ መቋቋማቸውን፣ በግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ከእምነት ተቋማት ጋር በጋራ እየሰሩ እንደሆነ፤ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ዙሪያ በ6 የሠፈራ ጣቢያዎች እየሠሩ እንደሚገኙ የተጎዱ ሴቶችን ወደ ሆስፒታል ሄደው እንዲታከሙ መደረጉን፣ በሴቶች ላይ ግርዛት ሲፈጽሙ የተገኙ ግለሰቦች ለፍርድ አቅርበው በአነስተኛ ቅጣት መለቀቃቸውን፣ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊት የሚጠቁ ሴቶች ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስገኙበት ስርዓት ያለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

85. በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የጅማ ዞን፣ የዞኑ የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ጽ/ቤት በተለይ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ የማተኮር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በየጊዜው እንደሚሰሩ፣ በተፈጥሮ አደጋ ዙሪያ የሚሠሩ ሥራዎች ከአደጋ መከላከል ጽ/ቤት ጋር እና ከተለያዩ መ/ቤቶች ከተውጣጡ ኮሚቴዎች ጋር በመሆን እደሚሳተፉ፣ የአጋሮ ከተማ የሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤት ከላይ የተጠቀሱት አደጋዎችና ድርጊቶች ሴቶች ሲጎዱ የሚደረግላቸው ሲሆን፣ ለምሳሌ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሲፈፀሙ ከቀበሌ ጀምሮ እስከ ላይ ያሉ ህግ አስፈጻሚ አካል ድረስ ደረጃ በደረጃ ከነዚህ አካሎች ጋር በመሆን መፍትሄ እንዲያገኙ የሚደረግና በህክምና ረገድም ድጋፍ የሚደረግላቸው መሆኑን፤ የጎማ ወረዳ የሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጽ/ቤት በአካባቢያቸው ይህን በኃላፊነነት የሚወጣ ተቋም የሌለ መሆኑ ይህን ሥራ ከነሱ ጋር ለመሥራት ፍቃደኛ የሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሌሉ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

86. በሰው ሰራሽም ሆነ  በተፈጥሮ አደጋዎች እንዲሁም በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለተጎዱ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሴቶች ትኩረት የሚያገኙበት ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አስቸኳይ ምላሽ ለመስጠት አያስችልም፡፡

## 2.2 በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ መፈጠሩንና ውጤታማነቱን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

### በሥርዓተ ጾታ ዙሪያ የተሰጠውን የግንዛቤ ማስጨባጫን በተመለከተ፣

87. ባህላዊ የሆኑ ፀረ ሴት አመለካከቶች ደረጃ በደረጃ እንዲቀሩ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡ በቤተሰብ ህጉ፣ በሴቶች ዙሪያ የወጡ ፖሊሲዎችና መርሀ ግብሮች አስመልክቶ በህብረተሰቡ ዘንድ በቂ ግንዛቤ የሚፈጠርበትና ተግባራዊነቱ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከልና ለማስወገድ ለጎሳ መሪዎች፣ ለሀይማኖት አባቶች፣ ለአካባቢ ሽማግሌዎችና ለማህበረሰብ ተቋማት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉና የሚታዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስቀረት የተካሄደው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ያስገኘው ለውጥ ሊገመገም ይገባል፡፡

88. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት እንደተቻለው በናሙና በተመረጡ የፌደራል መ/ቤቶች ውስጥ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ የግብርና ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ የፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ፣ የፌደራል ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን በሴቶች ዙሪያ በሚወጡ ህጎች እና ፖሊሲዎች ላይ የቤተሰብ ሕጉን ጨምሮ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን በተካሄደው ሥልጠናና ውይይት መሰረት የተፈለገውን ያህል በሴቶች ህይወት ዙሪያ ያለውን የተሳሳተ አመለካከት ላይ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣቱን በተመለከተ ግምገማ አልተከናወነም፡፡

89. በኦሮሚያ ክልል የክልሉ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶ ጉዳይ ቢሮ ለጅማ ዞን በሚገኙ ወረዳዎች በላከው መጠየቅ የተሰበሰበ መረጃ መሰረት፣ በዞኑ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ ጠለፋ፣ በጋብቻ ላይ ጋብቻ፣ ያላቻ ጋብቻ፣ የውርስ ጋብቻ፣ ድብዳባ፣ በየወረዳዎቹ በዋነኛነት የሚፈጸሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መሆናቸው፣ እነዚህን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ፈፅመው የተገኙ አካላት ወደ ህግ ያለማቅረብ እና ህብረተሰቡ እንዚህን ወገኖች እንደማያጋልጥ፣ በፍትህ አካላት በኩልም የግንዛቤ ችግር እንዳለ የተሰበሰበሰው መረጃ የሚያሳይ መሆኑን፣ በጅማ ዞን የጎማ ወረዳ የሴቶች ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በወረዳ ደረጃ ላሉ አመራሮች፣ ለሴቶች ጉዳይ ኃላፊዎች፣ ለኃይማኖት አባቶች እና ለሀገር ሽማግሌዎች በተለይ የጎጂ ልማዶችን ተመልክቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ቢሰጥም፣ አሁንም

የአመለካከት ችግር ያለና የወረዳው አመራሮች ጭምር በጋብቻ ላይ ጋብቻ የሚፈጽሙበት ሁኔታ እንዳለ ሲገልጹ፣ የአጋሮ ከተማ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ደግሞ ኋላ ቀር አመለካከትን ለማስቀረትና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ለመስራት የሀገር ሽማግሌዎችና የኃይማኖት አባቶችን ያካተተ ኮሚቴ መዋቅሩን ገልጸዋል፡፡

90. በጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የክልሉ የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ ሴቶች ጥቃት ደርሶባቸው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ለአቤቱታ ሲሄዱ የባልና የሚስት ጉዳይ አይመለከተንም በማለት ጥያቄአቸውን ተቀበሎ ያለማስተናገድ የሚታይ መሆኑን፣ በሴቶች ላይ ጥቃት አድርሠው በህግ ቁጥጥር ሥር የዋሉ ሠዎች ጉዳዩ ሳይጣራ የሚለቀቁበት ሁኔታ መኖሩን፣ የክልሉ የቤተሰብ ህግ ወጥቶ በዞን አመራር ደረጃ የተዋወቀ ቢሆንም፣ ወደ ወረዳና ቀበሌ ወርዶ ለህብረተሰቡ እንዲተዋወቅ ያልተደረገ መሆኑን፤ የአበቦ ወረዳ የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ጽ/ቤት ህብረተሰቡ ጐጂ ልማዳዊ ድረጊቶችን ለማጋለጥ ፍቃደኛ ያለመሆን፣ የተጐጂዋ ቤተሰብ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የመሸፋፈን ሁኔታ መኖር እና ተጐጂዎች ዘግይተው ለህግ ማቅረብ፣ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በወረዳው በስፋት ሰለሚፈፅሙ እዚህ ላይ ጠንክሮ መሥራት እንዳለበት እና በፍርድ የሚሠጠው ቅጣት አነስተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

91. የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራው ያመጣው ለውጥ በብዛትም ሆነ በጥራት የሚመዘንበት መለኪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩልም ሆነ በአስተባባሪነት የተሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ያስገኙት ለውጥን ወይም ውጤትን አስመልክቶ በመስክና በሪፖርት ከመከታተል ውጪ ያመጣው ለውጥ ወጥ በሆነ መልኩ የማይገመገም መሆኑ ታውቋል፡፡

92. ስለጉዳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሴቶችና ወጣቶች ንቅናቄ ተሳትፎ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በቀረበ መጠይቅ በተሰጠ ምላሽ፣ በ2003 ዓ.ም እነዚህን አካላት (ለጎሳ መሪዎች፣ ለሃይማኖት አባቶች፣ ለአካባቢ ሽማግሌዎችና ለማህበረሰብ ተቋማት ወዘተ) ክብርት ሚኒስትሯ በተገኙበት ሱማሌ ክልል ላይ ውይይት የተደረገ መሆኑን፣ ነገር ግን ክትትልን አስመልክቶ በመስክና በሪፖርት ከመከታተል ውጪ ለውጥ መጥቷል የሚለውን የምናይበት ሁኔታ የሌለ መሆኑን፣ ዘንድሮ ያመጣውን ለውጥ ለማወቅ ጥናት ለማካሔድ በዝግጅት ላይ እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡

93. በሴቶች ዙሪያ የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ህጎችና መርሃ ግብሮች ላይ ሚሰጠው የግንዛቤ ማስጨበጫ አፈጻጸም ደካማ መሆን እና የመጡትንም ለውጦች ለመለካት የሚያስችል ግልፅ መለኪያ ባለመቀመጡ በህብረተሰቡ ዘንድ ሴቶችን ዝቅ አድርገው የሚመለከቱና

የፆታ የበላይነትን የሚያንፀባርቁ አስተሳሰቦች፣ ባህልና ወግ ልምዶች አስወግዶ በአንፃሩ የእኩልነት አስተሳሰብ ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት አዳጋች ያደርጋል፡፡

<u>በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖሩ ሴቶች ገቢ በማስገኛ ሥራ ላይ እንዲሰሩ ለማድረግ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚነታቸውን በተመለከተ፣</u>

94. በገጠርና በከተማ የሚኖሩ ሴቶች ገቢ በማስገኛ ሥራ ላይ እንዲሰሩ ለማድረግ ብድር የሚያገኙበት ሥርዓት ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡ ሴቶችን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የግንዛቤ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ ሴቶች የብድር አገልግሎትን የሚመለከቱ መረጃዎች በአቅራቢያቸው እንዲያገኙ ሁኔታዎች ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡

95. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በጋምቤላ ብሔራዊ ክልል ውስጥ በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖሩ ሴቶች ገቢ በማስገኛ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ለማድረግ ብድር የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ በክልሉ አነስተኛ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ተቋም (Micro finance) ተቋቁሞ በተወሰኑ ወረዳዎች ላይ ፅ/ቤት የከፈተ ቢሆንም የሚያበድረው ለግለሰቦች ብቻ በመሆኑ ለተደራጁ የሴቶች ማህበራት የብድር አገልግሎት ባለመኖሩ ሴቶች ተጠቃሚ እንዳልሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

96. በኦዲቱ ወቅት በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን የተደራጁ ሴቶች ከኦሮሚያ የብድርና ቁጠባ ተቋም (ዋልቆ) የብድር ተጠቃሚ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

97. ስለጉዳዩ የጋምቤላ ክልል የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ፣ የአበቦ ወረዳ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት እና የከተማው የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊዎች በገቢ ማስገኛ ሥራ ላይ ለተደራጁ የሴቶች ቡድኖች ብድር አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ያልተመቻቸ መሆኑን፣ በክልሉ 38 የሴቶች ማህበራት ያሉ ሲሆን ጥቂቶቹ ከአደራጃቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅት (NGO'S)፣ ቀሪዎቹ ደግሞ በራሳቸው የግል መዋጮ ቆጥበው ሥራ የጀመሩ መሆናቸውን፤ የጋምቤላ ከተማ የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት በከተማው የአነስተኛ የቁጠባና የብድር ተቋም ያለ ቢሆንም የሚያበድረው ለግለሰቦች ብቻ መሆኑ ጽ/ቤቱ ያደራጃቸውን ማህበራት እየረዳ አለመሆኑና የከተማ ሴቶች ተጠቃሚ እንዳልሆኑ፤ የአበቦ ወረዳ የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት የቁጠባና ብድር ተቋማት በወረዳው ውስጥ የሌለ በመሆኑ የወረዳው ሴቶች የብድር ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ ያልተመቻቸላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

98. ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የብድር ሥርዓት በተጠናከረ መለኩ አለመዘርጋቱ የሴቶች ኢኮኖሚያዊ አቅም ለማጠናከር፣ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ እና ዕወቀትና ችሎታቻውን

በመጠቀም በተለያየ መስክ እንዲሰማሩ ለማደረግ የሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

<u>በስርዓተ ፆታ ጉዳይ ዙርያ የሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን በተመለከተ፣</u>

99. በስርዓተ ፆታ ጉዳይ ዙርያ የሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን እንቅስቀሴ ለመከታተል የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ የሚዘረጋውም የቁጥጥር ሥርዓት በፌዴራልና በክልል የሚገኙ የሚመለከታቸውን አካላት ሊያካትት ይገባል፡፡

100. የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከበጎ አድርጎት ኤጀንሲና ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት የፈቃድ አሰጣጥ፣ የክትትል እና የግምገማ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 621 አንቀጽ 67 የተደነገገ ቢሆንም እንቅስቃሴያቸውን ለመከታተልም ሆነ ለመገምገም የሚያስችል ስርዓት አልተዘረጋም፡፡

101. ስለጉዳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሴቶችና ወጣቶች ንቅናቄ ተሳትፎ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በቀረበ መጠይቅ በተሰጠ ምላሽ፣ በወጣው አዋጅ ቁጥር 621 አንቀጽ 67 የክትትሉና የግምገማው ሥልጣን የተሰጣቸው ቢሆንም፣ እስከ አሁን የተሰራው አንዱ ሥራ ብቻ እንደሆነ እሱም ኤጀንሲው ፕሮጀክት በሚልክ ጊዜ ተገምግሞ መስተካከል ያለበትን አስተያየት ሰጥተን ከመላክ ያለፈ ስራ አለመሰራቱን፣ ድርጅቶቹ ስልጣኑ እንዳላቸው እንኳ የማያውቁ መሆናቸውን፣ የመሠረታዊ የአሰራር ሂደት ጥናት (BPR) በሚጠናበት ጊዜ ዲፓርትመንት ሲቋቋም ይህ ጉዳይ ትኩረት አለመሰጠቱ፣ በአጠቃላይ የክትትልም ሆነ የግምገማ ስርዓት (System) ያልተዘረጋ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

102. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶችን የሚከታተልበት ሆነ የሚገመገሙበት ስርዓት ያለመኖሩ እነዚህ አካላት በትክክል ለተቋቋሙበት ዓላማ እየሰሩ ስለመሆናቸው ለማወቅ አያስችልም፡፡

<u>በሥርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶች መካከል የሚካሄድ የልምድ ልውውጥን በተመለከተ፣</u>

103. ሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የተለያዩ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶች የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የሚዘረጋውም ሥርዓት በሥርዓተ ጾታ ጉዳይን ለመተግበር በሚያደርጉት ጥረት መልካም ተሞክሮ ባላቸው ክልሎች፣ ማህበራት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች በየአመቱ የልምድ ልውውጥ ሊደረግና ሊገመገም ይገባል፡፡

104. በኦዲቱ ወቅት የሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ ባሉ ዋና ዋና አስፈጻሚ መ/ቤቶች እና ክልሎች ጋር የልምድ ለውውጥ የሚደረግበት የምክክር መድረክ ዘርግቶ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ነገር ግን ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ የተለያዩ በሴቶች ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር የልምድ ልውውጥ የሚደረግብት ስርዓት ያለመዘርጋቱ ታውቋል፡፡

105. በናሙና ከተመረጡ የፌደራል መ/ቤቶች፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና በውኃና ኢነርጂ ሚኒስቴር በሥራቸው ካሉ ተጠሪ መ/ቤቶች እና ከክልል ሴክተር ቢሮዎች ተጠሪዎች ጋር በየሩብ ዓመቱና በየስድስት ወር በሚኖር የውይይት መድረክ ልምድ የሚለዋወጡ ሲሆን፣ ነገር ግን ለልምድ ልውውጥ ተብሎ የሚዘጋጅ መድረኮች የሌሉ መሆኑን፤ የፌደራል ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ፣ የፌደራል ፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ሰራተኛ ማህበር ኮንፌደሬሽን፣ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ጅማ ዞን የጎማ ወረዳ ሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት፣ በጋምቤላ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት የጋምቤላ ከተማ መስተዳደር የሴቶች ህጻናት ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት፣ የአበቦ ወረዳ የሴቶች ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ጽ/ቤት የልምድ ልውውጥ የማይከናወን መሆኑን ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ መልስ ሰጥተዋል፡፡

106. ስለጉዳዩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሴቶችና ወጣቶች ንቅናቄ ተሳትፎ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው፣ GO-NGO በሚል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የፌደራል ሴክተር መ/ቤቶች ፎረምን ያካተተ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሰብሳቢነት እንዲቋቋም እየታሰበ ያለበት ሁኔታ እንዳለ ገልፀዋል፡፡

107. የተለያዩ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ አካላት መካከል እርስ በእርሳቸው የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበት ስርዓት አለመኖሩ የተሻለ (ምርጥ) ተሞክሮዎችን በመቀምር እንዳይስፋፉ ያደርጋል፡፡

## 2.3 በስርዓተ ፆታ ጉዳይ ዙሪያ የተሟላ የመረጃ ፍሰት ስርዓት መኖሩን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

### ከሥርዓተ ጾታ ጋር የተያያዙ ጥናቶችና መረጃዎች አያይዝን በተመለከተ፣

108. በአገሪቱ ውስጥ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች ሊሰበሰቡና በመረጃነት የሚያዙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ ስርዓተ ፆታን የተመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡ በመስክ የተገኙ መረጃዎችና ከአስፈፃሚ አካላት የሚሰበሰቡ ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶች መጠናቀር አለባቸው፡፡ የተጠናቀሩት ሪፖርቶች ሊተነተኑና እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡ የስርዓተ ፆታ ጉዳይ ላይ በሚሰሩ አካላት መካከል የመረጃ ልውውጥ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስርዓተ ፆታን የሚመለከቱ መረጃዎችን በመረጃ መረብ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ የመረጃ መረቡም በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

109. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በታዩ የፌዴራል አስፈጻሚ መ/ቤቶች፣ በኦሮሚያ እና በጋምቤላ ክልል የሚገኙ ዞኖችና ወረዳዎች ውስጥ ከሥርዓተ ጾታ ጋር የተያያዙትን አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ላይ የአያያዝ ችግር መኖሩ፣ በሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ፣ የተለያዩ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚካሄዱ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሁኔታንና ለተጠቃሚዎች ያስገኙትን ፋይዳ የሚመለከቱ መረጃዎች ተደራጅተው ያልተቀመጡ መሆኑ ታውቋል፡፡ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን በተመለከተ የችግራቸውን አይነት፣ ስፋትና ጥልቀት በትክክል የሚያሳይና ለመፍትሔ እርምጃ ሊያግዝ የሚያስችል መረጃ ከቀበሌና ከወረዳ ጀምሮ በየደረጃው እየተጠናቀረ በማእከል የሚያዝበት ስርዓት እንደሌለ በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

110. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጠውን ሃላፊነት ለመወጣት በሴቶች ሁለንተናዊ ደህንነት ዙሪያ አስፈላጊ መረጃዎች ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀትና ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል የመረጃ ፍሰት ስርዓት ስለመዘርጋቱና ተግባራዊ ስለመደረጉ እና ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ ሥርዓተ- ጾታን የሚመለከቱ መረጃዎችን አሰባስቦና አደራጅቶ ለግብአትነት ለመጠቀም እና ለሌሎች መረጃውን ለተለያየ ግብዓት ለሚፈልጉ አካላት በቀላሉ የሚያገኙበትም ሆነ የሚሰራጭበት መንገድ ለማመቻቸት የሚያስችል የመረጃ አያያዝና አቅርቦት ሥርዓት ስለመዘርጋቱ መረጃ አልቀረበም፡፡

111. ከተለያዩ ክልሎችና ከፌዴራል አስፈፃሚ አካላት የሚሰበሰቡ ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የልምድ ልውውጦች እና በመስክ ጉብኝት የሚገኙ መረጃዎች የሚጠናቀሩበት፣ የሚተነተኑበትና እርምጃ የሚወሰድበት ሥርዓት የለም፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሴቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በመረጃ መረብ (web site) ለማሰራጨት የሚያግዝ የመረጃ መረብ አልተዘረጋም፡፡

112. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ብዙ ልምድ ልውውጦች የሚካሄዱ መሆኑና ነገር ግን ተቀምረው በመፅሀፍ ወይም በሥልጠና መልክ የሚሰጥበት ሁኔታ የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

113. በአጠቃላይ የተለያዩ መረጃዎችን በዓይነትና በጾታ ለይቶና አደራጅቶ ለጥቅም በማዋል በኩል ያለው ችግር ሰፊ መሆኑን መረጃ የሚሰበሰበው እንደሌሎች መረጃዎች ከአንድ አካል/ ሴክተር ብቻ ሳይሆን ከላይ እስከታች ከሁሉም አካላት/ ሴክተር መ/ቤቶች መሆኑ፣ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ለማደራጀትና ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ ከላይ እስከ ታች ድረስ የአቅም ውስንነት መኖር፣ የመረጃ መሰረተ ልማቶች( IT Infrastructure) በአግባቡ አለመደራጀት… ወዘተ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች የተለያየ ፍላጎትና ችግር ያለባቸው መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅተዋል ለማለት የሚያስቸግር እንደሆነ፣ አሁን ግን ከመጋቢት 2003 ዓ.ም. ጀምሮ የኢንፎርሜሽን ቴክሎጂ (IT) እና የመረጃ ልማት ዳይሬክቶሬት የተቋቋመ በመሆኑ መረጃው የሚጠናቀርበት ሁኔታ እንደሚመቻች፣ ይህ ሲባል ግን በተበታተነና ባልተደራጀ መልኩ በየክልሉ በሚመለከታቸው አካላት መረጃዎች የሉም የሚል ድምዳሜ አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡

114. ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም የመረጃና የሪፖርት ልውውጡን ፈጣን ለማድረግ መ/ቤታቸው ከክልሎች ጋር በመረጃ መረብ ለማገናኘት (Networking)፣ የመረጃ ቋት(Data base) ለመመስረት እንዲሁም ድህረ ገጽ (Web page) ለመክፈት ከፍተኛ እንቅስቃሴ መጀመሩን ገልፀዋል፡፡

115. በአገሪቱ ውስጥ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች፣ በመስክ የተገኙ መረጃዎችና ከአስፈፃሚ አካላት የሚሰበሰቡ ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶች ተጠናቅረው እርምጃ የሚወሰድበት ስርዓት ያለመኖሩ እና ስርዓተ ፆታን የሚመለከቱ መረጃዎችን በመረጃ መረብ እንዲሰራጭ ያለመደረጉ በሥርዓተ ጾታ ጉዳዮች ላይ ለሚወጡ ፖሊሲዎችና ጥናቶች በተሟላና ወቅታዊ መረጃዎች ላይ እንዳይመሰረቱ ያደርጋል፡፡

**የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ በዕቅዶች ውስጥ ተካተው መተግበራቸውን የሚያሳይ ሪፖርት መቅረቡን በተመለከተ፣**

116. ሥርዓተ ፆታን ሜይንስትሪሚንግ ያደረጉ የፌደራል መ/ቤቶች፣ ድርጅቶች እና ክልሎች በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ በየሩብ አመቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

117. ሥርዓተ ፆታን ሜይንስትሪም ያደረጉ የፌደራል መ/ቤቶች፣ ድርጅቶች እና ክልሎች በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ በየሩብ አመቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት የሚደረግ መሆኑ ቢገለፅም በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2000-2003 ዓ.ም ያለውን ከክልል የተላኩ ሪፖርቶች እንዲያቀርቡ ተጠይቆ፣ መረጃው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ደረስ አልቀረበም፡፡

118. ከክልል የሚሰበሰቡ ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶች በአግባቡ ተሰብስበው ባለመያዛቸው በየወቅቱ የሚፈለጉት ስራዎች ለመሰራታቸው ለመከታተል፣ የሚላኩትን የአፈፃፀም ሪፖርቶች ለማነፃፀርና እርምጃ ለመውሰድ አያስችልም፡፡

# ክፍል ሦስት፡

## መደምደሚያዎች

119. የስርዓተ ፆታን ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣ በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተቱንና ተግባራዊነቱን በተመለከተ፣

- የሴቶች ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ እንዲካተት ለማድረግ የሚያግዝ የማስፈፀሚያ ሰነድን (Gender Mainstreaming Guide line) በሚኒስቴር መ/ቤቱ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተዘጋጀው ለፌዴልና እና ለክልል አስፈፃሚ አካላት አለመሰራጨቱ፣ ስልጠናውን የተሳተፉ ሰዎች የማስፈፀሚያ ሰነዱን ለተወከሉበት መ/ቤት አለማስተላለፋቸው፣

- ሀገር አቀፍ የማስፈፀሚያ ሰነድ (Guide line) መሰረት አድርገው የራሳቸውን የማስፈፀሚያ ሰነድ ያላዘጋጁ የፌዴራል መ/ቤቶችም ሆነ ክልሎች ያሉ መሆኑና የማስፈፀሚያ ሰነዱን የማያውቁት የፌዴራል መ/ቤቶችም ሆነ የክልል ቢሮዎች ያሉ መሆኑ፣

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የስርአተ ጾታ ጉዳዮች በፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተገቢው መልኩ መተንተናቸውንና በየስራው ዘርፍ መካተታቸውን የሚረጋገጥ ለመሆኑ መረጃ አለመቅረቡ፣

- በየተቋማቱ ዕቅድ ሲዘጋጅ ግብን ከማስቀመጥ ባለፈ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂ ስልትም ሆነ መለኪያ እንዲሁም ግብ የማያስቀምጡና ክትትል እና ግምገማም የማያካሂዱ መሆኑን፣

- የስርዓተ ፆታ ጉዳይ መካተቱን ከዕቅድ እስከ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ የማያከናውኑ የፌዴራልም ሆነ የክልል መ/ቤቶች መኖራቸው፣

- የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በደረጃ እድገት፣ በዝውውር፣ በኮሚቴ አወቃቀር፣ ስንብትና ስልጠና ላይ መካተቱና ያስገኘው ውጤት ምን እንደሆነ በየጊዜው የማይገመገም መሆኑ፣

- ቀደም ሲል የደረጃ እድገት ዝውውር እና ቅጥርን በሚመለከት የስርዓተ ፆታ ክፍል ቀጥተኛ ተሳታፊ የነበረ መሆኑ የታወቀ ሲሆን፣ በ2000 ዓ.ም. በሲቪል ሰርቪስ በወጣ መመሪያ መሠረት የኮሚቴ አሠራር በመቅረቱ በየጊዜው የሚካሄደውን ሁኔታ እንደቀድሞ የሴቶችን ተጠቃሚነት ባገናዘበ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን አለመረጋገጡ፣

- ሥርዓተ ፆታን የሚመለከት አካል በመዋቅር ደረጃ ተዋቅሮ በግልጽ የሚታይ ቢሆንም ሥራው በተጠሪ (focal person) እንደተደራቢ የሚያሰሩ መኖራቸው፣ መዋቅሩ የሌለ እና በተጠሪ እንዳስፈላጊነቱ ሥራው የሚሰሩ መ/ቤቶች መኖራቸው፣
- በቦታው ላይ ለተመደቡ ሰዎች ከሚመደብ የደሞዝ በጀት ውጪ ለስራ ማስኬጃ የሚሆን (በስርዓተ ፆታ ዙሪያ ለሚሰሩ ስራዎች) በጀት የማይመደብ እና ቢሮና ቁሳቁስ ያልተሟላላቸው አስፈጻሚ መ/ቤቶች መኖራቸው፣
- አገሪቱ በሥርዓተ ጾታ ዙሪያ የገባቻቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች/ ኮንቬንሽኖቹ ለፌዴራልና ለክልል አስፈጻሚ አካላት ያልተዋወቁና ተለይተው አለመያዛቸው፣
- ስርዓተ ፆታን የተመለከቱ ጥናቶች በአብዛኛው በፌዴራልም ሆነ በክልል ቢሮዎች የማይጠኑ መሆናቸው እና የተወሰኑ የተጠኑ ጥናቶችም ስራ ላይ ስለመዋላቸው መረጃ አለመቅረቡ፣
- የስርዓተ ፆታን ጉዳይ አስመልክቶ በተለያዩ አካላት የሚከናወኑ ፕሮግራሞች በቅንጅት የማይታቀዱ፣ ክትትልና ግምገማ የማይከናወን መሆኑ፣
- በክልሎች፣ በዞኖችና ወረዳዎች የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ (ጽ/ቤት) ጋር ስምምነት ለመፈራረም ሲንቀሳቀሱ የክልሎችንም ሆነ የዞንና የወረዳ የሴትና ሕጻናት ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች የማያሳውቁ መሆኑ፣
- የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከበጎ አድርጎት ኤጀንሲና ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት የፈቃድ አሰጣጥ፣ የክትትል እና የግምገማ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 621 አንቀጽ 67 የተደነገገ ቢሆንም እየተሰራ ያለው ግን ኤጀንሲው ፕሮጀክት ሲልክ ከመገምገም ባለፈ እንቅስቃሴያቸውን ለመከታተልም ሆነ ለመገምገም የሚያስችል ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣

120. በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ መፈጠሩንና ውጤታማነቱን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

- የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና እና የተለያዩ መድረኮች በሴቶች ህይወት ላይ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣቱን በተመለከተ ግምገማ አለመከናወኑ፣ እንዲሁም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራው ያመጣው ለውጥ በብዛትም ሆነ በጥራት የሚመዘንበት መለኪያ አለመዘጋጀቱ፣
- የተለያዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በየወረዳዎች የሚፈፀሙ መሆኑ፣

- በህብረተሰቡ፣ በህይማኖት አባቶች፣ በሀገር ሽማግሌዎች፣ በፍትህ አካላት በኩል የሥርዓተ ጾታን በተመለከተ የግንዛቤ ችግር መኖሩ፣
- በጎጂ ልማዳዊ ድርጊት የሚጠቁ ሴቶች ድጋፍና እንክብካቤ የሚያገኙበት ስርዓት በየደረጃው ተዘርግቶ ተግባራዊ ያለመደረጉ፣
- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የተለያዩ በሴቶች ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶች የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበት መድረክ ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- በጋምቤላ ብሔራዊ ክልል ውስጥ በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖሩ ሴቶች ገቢ በማስገኛ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ለማድረግ ብድር የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በተለያየ መልክ የሚገቡ ፈንዶች ምንጫቸውና ለምን ዓላማ እንደተገኙ የጊዜ ገደባቸውን ጨምሮ በሚገልጽ መንገድ ተለይተው አለመያዛቸው፣ ፈንዶቹ ለታለመላቸው ዓላማና ተግባር መዋላቸው የሚረጋገጥበት እና የሚገመገምበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያለመደረጉ፣

121. በስርዓተ ፆታ ጉዳይ ዙሪያ የተሟላ የመረጃ ፍሰት ስርዓት መኖሩን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

- በሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ፣ የተለያዩ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚካሄዱ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሁኔታን፣ ለተጠቃሚዎች ያስገኙትን ፋይዳ የሚመለከቱ መረጃዎች ተደራጅተው ያልተቀመጡ መሆኑ፣
- በሴቶች ሁለንተናዊ ደህንነት ዙሪያ አስፈላጊ መረጃዎች ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀትና ስራ ላይ ለማዋል የሚያሰችል የመረጃ ፍሰት ስርዓት ያለመኖሩ፣
- ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ ሥርዓተ- ጾታን የሚመለከቱ መረጃዎችን አሰባስቦና አደራጅቶ ለግብአትነት ለመጠቀም እና ለሌሎች መረጃውን ለተለያየ ግብዓት ለሚፈልጉ አካላት በቀላሉ የሚያገኙበትም ሆነ የሚሰራጭበት መንገድ ለማመቻቸት የሚያችል የመረጃ አያያዝና አቅርቦት ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገሪቱ ስርዓተ ፆታን የሚመለከቱ መረጃዎችን በመረጃ መረብ (web site) ለማሰራጨት የሚያግዘው የመረጃ መረብ ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- ከተለያዩ ክልሎችና ከፌዴራል አስፈፃሚ አካላት የሚሰበሰቡ ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የልምድ ልውውጦች እና በመስክ ጉብኝት የሚገኙ መረጃዎች

የሚያዙበት፣ የሚጠናቀሩበት፣ የሚተነተኑበትና እርምጃ የሚወሰድበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያለመደረጉ፣

- በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በሌሎች በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ አስፈጻሚ አካላት የሴቶችን ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት የሚገታ እና አገሪቱ ወደፊት ልትደርስበት ከታሰበው እድገት ለምታደርገው እንቅስቃሴን እንቅፋት ይሆናል፡፡

122. በአጠቃላይ በአገሪቱ የስርዓተ ፆታን እኩልነት ለማረጋገጥ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሌሎች የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላት ጋር በመቀናጀትና በማስተባበር በርካታ ሥራ መስራቱ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ ተካቶ በአግባቡ ሥራ ላይ ካልዋለ እንዲሁም ተግባራዊነቱ የሚያረጋግጥ ጠንካራ የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ካልተዘረጋ የተጀመረው የሴቶችን በሁሉም ዘርፍ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚሰራው ሥራ ስኬታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድር በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ያሻሽላሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት፡

## የማሻሻያ ሀሳቦች

123.የስርዓተ ፆታን ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣ በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተቱንና ተግባራዊነቱን በተመለከተ፣

- የሴቶች ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ እንዲካተት ለማድረግ የሚያግዝ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ያዘጋጀው የማስፈፀሚያ ሰነድ (Gender Mainstreaming Guide line) ለፌዴራል እና ለክልል አስፈፃሚ አካላት ሊሰራጭ፣ ሊተዋወቅና ከየሥራ ዘርፋቸው ሁኔታ ጋር በማጣጣም የራሳቸውን የማስፈጸሚያ ማንዋል እንዲያዘጋጁ ድጋፍና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ በስልጠና ወቅት የተሰጡ ሰነዶች የስልጠና ተሳታፊዎች ተወክለው ለመጡበት ተቋም ማድረሳቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የስርአተ ጾታ ጉዳዮች በፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተገቢው መልኩ መተንተናቸውንና በየስራው ዘርፍ መካተታቸው የሚረጋገጥበት የአፈፃፀም መለኪያ ሊዘጋጅ፣ ክትትልና ግምገማ ሊካሄድ ይገባል፡፡
- የደረጃ እድገት፣ የዝውውር፣ የኮሚቴ አወቃቀር፣ ስንብትና ስልጠናን በአጠቃላይ ሴቶች በሁሉም ዘርፍ ከወንዶች እኩል ዕድል የሚያገኙበትና ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ ሊመቻችላቸውና በየጊዜው ያለውን ለውጥ ሊገመገምና በሚታዩ ክፍተቶች ወዲያውኑ እርምጃ የሚወሰድበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- የደረጃ እድገት ዝውውር እና ቅጥርን በሚመለከት በሲቪል ሰርቪስ በወጣ መመሪያ መሠረት የስርዓተ ፆታ ክፍል ቀጥተኛ ተሳታፊ ስላልሆኑ በየጊዜው የሚካሄደውን ሁኔታ እንደቀድሞ የሴቶችን ተጠቃሚነት ባገናዘበ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን የሚፈተሸበት ሥርዓት ተዘርገቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የስርዓተ ፆታ ክፍል በሁሉም የፌዴራል መ/ቤቶች፣ በክልሎች እና በስራቸው በሚገኙ ከተሞች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች በሚገኙ የመንግስት መ/ቤቶች በመዋቅር ደረጃ በግልፅ ሊቋቋሙ፣ በመዋቅሩ መሰረት የሚያስፈልገው የሰው

ኃይል፣ ለስራ ማስኬጃ የሚሆን (በስርዓተ ፆታ ዙሪያ ለሚሰሩ ስራዎች) በጀት እና ቢሮና ቁሳቁስ ሊሟላላቸው ይገባል፡፡

- ሀገራችን በሴቶች ዙሪያ የገባቻቸውን ስምምነቶች ከላይ ጀምሮ እስከ ወረዳ እና ቀበሌ ድረስ ላሉት መዋቅሮች እና ለህብረተሰቡ ሊተዋወቁ፣ ሊሰራጩና በመረጃነት ሊያዙ ይገባል፡፡
- አገሪቱ አለም አቀፍ ግዴታ የገባችባቸው እነዚህ ስምምነቶቹ ብቻቸውንም ሆነ ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ውስጥ ተካተው ስራ ላይ እንዲውሉና ያስገኘውን ውጤት አስመልክቶ የክትትልና የግምገማ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በፌዴራልም ሆነ በክልል ቢሮዎች ወንዶችንና ሴቶችን በሀገሪቱ የልማት ፖሊሲዎች፣ ፕሮራሞችና ፕሮጀክቶች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸውና በእኩልም ደረጃ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ ያሉ ክፍተቶችን ለመለየት የሚያስችሉ ጥናቶች በየጊዜው ሊጠኑና በጥናቱም መሰረት እርምጃ የሚወሰድበት ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚጠኑ ጥናቶች ሲጠኑ ከታቸለ በመጀመሪያ ጥናቱ በአማርኛ እንዲዘጋጅ ሊደረግ ከአቅም በላይ ሆኖ በእንግሊዘኛና በሌሎች የውጭ ቋንቋዎች የሚጠኑም ከሆነ ሁሉም ሊረዳውና ሊተገብረው በሚችለው ወደ ፌዴራልና የክልል የስራ ቋንቋ ተተርጉሞ ለሚመለከታቸው አካላት ሊሰራጭና ሊተዋወቅ ይገባል፡፡
- የስርዓተ ፆታን ጉዳይ አስመልክቶ በተለያዩ አካላት የሚከናወኑ ፕሮግራሞች በቅንጅት የሚታቀድበት እና አፈፃፀሙን በተመለከተ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በፌዴራልም ሆነ በክልል ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በክልሎች፣ በዞኖችና ወረዳዎች የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ (ጽ/ቤት) ጋር ስምምነት ለመፈራረም ሲንቀሳቀሱ የክልሎችንም ሆነ የዞንና የወረዳ የሴትና ሕጻናት ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች ሊያውቁትና ድርጅቶች በተቋቋሙበት ፈቃድ በጠየቁበት ዕቅድና ፕሮግራም መሰረት እየሰሩ ስለመሆናቸው ክትትል ቁጥጥርና ግምገማም ሊካሄድ ይገባል፡፡

- የሚኒስቴር መ/ቤቱ ከበጎ አድርጎት ኤጀንሲና ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ፈቃድ ከመስጠት ጀምሮ እንቅስቃሴያቸውን ለመከታተልም ሆነ ለመገምገም የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

124.በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ መፈጠሩንና ውጤታማነቱን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

- በአገሪቱ ውስጥ በሴቶች ዙሪያ የወጡ ፖሊሲዎች፣ ህጎችና መርሀ ግብሮች፣ የቤተሰብ ህጉን፣ ባህላዊ የሆኑ ፀረ ሴት አመለካከቶችን፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉና የሚታዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስቀረት ለህብረተሰቡ (ለፍትህ አካላት፣ ለጎሳ መሪዎች፣ ለሃይማኖት አባቶች፣ ለአካባቢ ሽማግሌዎችና ለማህበረሰብ ተቋማት ወዘተ) ተከታታይነት ባለው መልኩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሰራና የመጣውን ለውጥ በየጊዜው የሚገመገምበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በጎጂ ልማዳዊ ድርጊት የሚጠቁ ሴቶች ድጋፍና እንክብካቤ የሚያገኙበት ስርዓት በየደረጃው ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የተለያዩ በሴቶች ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶች የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በጋምቤላ ብሔራዊ ክልል ውስጥ በገጠርም ሆነ በከተማ ለሚኖሩ ሴቶች ገቢ በማስገኛ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ለማድረግ ብድር የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በተለያየ መልክ የሚገቡ ፈንዶች ምንጫቸውን፣ ለምን ዓላማ እንደተገኙ፣ የጊዜ ገደባቸውን ጨምሮ በሚገልጽ መንገድ ተለይተው በመረጃነት ሊያዙና ፈንዶቹ ለታለመላቸው ዓላማና ተግባር መዋላቸው የሚረጋገጥበት እና የሚገመገምበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

125. በስርዓተ ፆታ ጉዳይ ዙሪያ የተሟላ የመረጃ ፍሰት ስርዓት መኖሩን ማረጋገጥን በተመለከተ፣

- በሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ፣ የተለያዩ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚካሄዱ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሁኔታን፣ ለተጠቃሚዎች ያስገኙትን ፋይዳ የሚመለከቱ መረጃዎች ተደራጅተው ሊቀመጡ ይገባል፡፡

- በሴቶች ሁለንተናዊ ደህንነት ዙሪያ አስፈላጊ መረጃዎች ለማሰባሰብ፣ ለማደራጀትና ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል የመረጃ ፍሰት ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡
- ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ ሥርዓተ- ጾታን የሚመለከቱ መረጃዎችን አሰባስቦና አደራጅቶ ለግብአትነት ለመጠቀም እና ለሌሎች መረጃውን ለተለያየ ግብዓት ለሚፈልጉ አካላት በቀላሉ የሚያገኙበትም ሆነ የሚሰራጭበት መንገድ ለማመቻቸት የሚያችል የመረጃ አያያዝና አቅርቦት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ከተለያዩ ክልሎችና ከፌዴራል አስፈፃሚ አካላት የሚሰበሰቡ ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የልምድ ልውውጦች እና በመስክ ጉብኝት የሚገኙ መረጃዎች የሚያዙበት፣ የሚጠናቀሩበት፣ የሚተነተኑበትና እርምጃ የሚወሰድበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሴቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በመረጃ መረብ (web site) ለማሰራጨት የሚያግዘው የመረጃ መረብ ሊዘረጋ ይገባል፡፡

126. በአጠቃላይ በአገሪቱ ሴቶች በማናቸውም ዓይነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ተሳታፊነታቸውንና ተጠቃሚነታቸውን ለማስጠበቅ ብሄራዊ ህጎች፣ ፖሊሲዎችና በዘርፉ የወጡ አለም አቀፍ ስምምነቶችን ጥናትን መሰረት በማድረግ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግና አፈፃፀማቸውን ለመከታተል የተጠናከረ የክትትል እና የግምገማ ሥርዓት ለመዘርጋት እና ተግባራዊ ለማድረግ የሚኒስቴር መ/ቤቱን፣ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ የፌዴራል እና የክልል አስፈጻሚ አካላት እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል፡፡ ይህንንም ለማሳካት በፌዴራል እና በክልል የሚገኙ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት ተቆጣጣሪ አካላት ከፍተኛ ሚና እደሚኖራቸው ይታመናል፡፡ በዚህ ሪፖርት የተገለጹት ግኝቶች፣መደምደሚያዎች እና የማሻሻያ ሃሳቦች በቀጥታ ሚኒስቴር መ/ቤቱን የማይመለከቱ ቢኖሩ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ስለሚያግዘው በተጠቀሱት ችግሮች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሃሳቦች ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በማሳወቅ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

በመጨረሻም የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር፣ እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት መረጃ የተሰበሰበባቸው የፌዴራል እና የክልል፣ የዞን እና የወረዳ መ/ቤቶች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

**አባሪ 1**

| የኦዲት ጭብጥ (Issues) | የመገምገሚያ መስፈርት (Evaluative criteria) |
|---|---|
| 1. የሴቶች ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣ በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተቱንና ተግባራዊነቱን ማረጋገጥ | 1.1 የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በሁሉም ዘርፍ እንዲካተት ለማድረግ የሚያግዙ የማስፈፀሚያ ሰነዶች (ማንዋሎች) ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 1.2 የተዘጋጁትም የማፈጸሚያ ሰነዶች ለሚመለከታቸው አካላት ሊተዋወቅና ሊሰራጭ ሊሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 1.3 የሰነዶቹ ተግባራዊነትና ያስገኙት ውጤት ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| | 1.4 በየደረጃው የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በውስጣቸው እንዲካተቱ ለማድረግ የሚዘጋጁ የተለያዩ ዕቅዶች (ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች) እና የማስፈጸሚያ ሰነዶች (ማንዋሎች) ወደ የክልሉ የሥራ ቋንቋዎች ሊተረጎሙ ይገባል፡፡ |
| | 1.5 የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በባለቤትነት የሚከታተል አካል በሁሉም የመንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሊቋቋም ይገባል፡፡ |
| | 1.6 በመንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ለሚቋቋሙ የስርዓተ ፆታ ጉዳይ የኃላፊነትና የተጠያቂነት ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 1.7 በመንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የስርዓተ ፆታን ጉዳይ ለሚከታተል አካልና ስርዓተ ፆታን በተመለከተ ለሚታቀዱ ስራዎች በጀት፣ ቢሮና ቁሳቁስ ሊሟሉላቸው ይገባል፡፡ |
| | 1.8 የማስፈፀሚያ ሰነዶች(ማንዋሎች)፣ የክህሎት ስልጠናዎች፣ የልምድ ልውውጦች፣ አለም አቀፍና አህጉራዊ ኮንቬንሽኖች፣ ስምምነቶችና ቻርተሮች በተግባር ውለው ያስገኙትን ውጤት አስመልክቶ ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ ሊካሄድ ይገባል፡፡ |
| | 1.9 የስርዓተ ፆታን ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣ በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እንዲካተት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሞያዊ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 1.10 የስርዓተ ፆታ ጉዳይ በስትራቴጂዎች፣ በእቅዶች፣በፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተቱ ያስገኘውን ውጤት የሚገመገምበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.11 ሀገራችን በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ የገባችውን አለም አቀፍ ስምምነቶች/ ኮንቬንሽኖች ተለይተው ሊያዙ ይገባል፡፡ |
| | 1.12 ስምምነቶቹም በየደረጃው ለሚመለከታቸው አካላት ሊተዋወቁ ይገባል፡፡ |
| | 1.13 ሥራ ላይ እንዲውሉ የሚደረግበትም ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ |
| | 1.14 ተግባራዊነታቸውና ያስገኙት ውጤት በየዓመቱ ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| | 1.15 ከሴቶች ጋር በተያያዘ በተለያዩ ብሔረሰቦች ያለውን አመለካከትና ልምድ አስመልክቶ ጥናት ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.16 የስርዓተ ፆታን ጉዳይ አስመልክቶ በተለያዩ አካላት የሚከናወኑ ፕሮግራሞች ተደራራቢ እንዳይሆኑ በቅንጅት የሚታቀድበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደግ ይገባል፡፡ |
| | 1.17 ሴቶች በእኩልነት ላይ በተመሰረተ የደረጃ እድገት፣ ዝውውር፣ የኮሚቴ አወቃቀር፣ ስንብትና ስልጠና የማግኘትና ተጠቃሚ የመሆን መብታቸው መጠበቁን ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.18 በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ አደጋዎች ለተጎዱ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሴቶች ትኩረት የሚያገኙበት ሥርዓት መዘርጋት አለበት፡፡ |
| | 1.19 በገጠር የሚኖሩ ሴቶች ገቢ በማስገኛ ሥራ ላይ እንዲሰሩ ለማድረግ ብድር የሚያገኙበት ሥርዓት ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡ |
| | 1.20 ከስርዓተ ፆታ ጋር በተያያዘ በተለያየ መልክ የሚገቡ ፈንዶች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ተመዝግበው ሊያዙ ይገባል፡፡ |
| | 1.21 ፈንዶቹም ለተባለላቸው ተግባር መዋላቸውን የሚረጋገጥበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.22 በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የተጎዱ ሴቶች የድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎት የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.23 የሚዘረጋውም ሥርዓት የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 1.24 ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን መፈፀምን የገቢ ምንጭ ያደረጉ ግለሰቦች በሌሎች የገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሊሠራ ይገባል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| | 1.25 | እነዚህ ግለሰቦች በሌላ ገቢ የማስገኛ የሥራ መስክ የሚሰማሩበት ሁኔታ ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡ |
| | 1.26 | በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድሎዎች በጥናት ሊለዩ ይገባል፡፡ |
| | 1.27 | በጥናት የተለዩት መድልዎች የሚወገዱባቸውን የመፍትሔ ሀሳቦች በማቅረብ ተግባራዊ መደረጉ መረጋገጥ አለበት፡፡ |
| | 1.28 | የፌዴራልና የክልል መ/ቤቶች፣ የሴቶች ጉዳይ ቢሮዎች/ ጽ/ቤቶችና መምሪያዎች የአቅም ክፍትት ጥናት ሊያካሄድ ይገባል፡፡ |
| | 1.29 | በሴቶች ላይ የሚፈፀም የኃይል ጥቃት ለመለየት የሚያስችል ጥናት ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 1.30 | በሴቶች ጉዳይ ዙርያ የሚሰሩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን እንቅስቀሴ ለመከታተል የሚስችል የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| 1. በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ መፈጠሩንና ውጤታማነቱን ማረጋገጥ | 2.1 | ባህላዊ የሆኑ ፀረ ሴት አመለካከቶች ደረጃ በደረጃ እንዲቀሩ፣ የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 2.2 | መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የተለያዩ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ ድርጅቶች የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበት መድረክ ሊፈጠር ይገባል፡፡ |
| | 2.3 | በቤተሰብ ምጣኔ አጠቃቀምና አስፈላጊነት ላይ ወንዶችና ሴቶች ግንዛቤ የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.4 | ሴቶችን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የግንዛቤ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 2.5 | ሴቶች የብድር አገልግሎትን የሚመለከቱ መረጃዎች በአቅራቢያቸው እንዲያገኙ ሁኔታዎች ሊመቻችላቸው ይገባል፡፡ |
| | 2.6 | በቤተሰብ ህጉ ላይ ለህብረተሰቡ(በተለይ ለሴቶች) የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ሊሰሩ ይገባል፡፡ |
| | 2.7 | የተሰራው የግንዛቤ ማስጨበጫ ያመጣው ለውጥ በየዓመቱ ሊገመገም ይገባል፡፡ |
| | 2.8 | ሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከልና ለማስወገድ ለጎሳ መሪዎች፣ ለሀይማኖት አባቶች፣ ለአካባቢ ሽማግሌዎችና ለማህበረሰብ ተቋማት በየአመቱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 2.9 | በሴቶች ዙሪያ የወጡ ፖሊሲዎች፣ ህጎችና መርሀ ግብሮች አስመልክቶ በህብረተሰቡ ዘንድ በቂ ግንዛቤ የሚፈጠርበትና ተግባራዊነቱ የሚረጋገጥበት ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ |
| | 2.10 | በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉና የሚታዩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስቀረት የተፈጠረ ግንዛቤ፣ የተገኘው ለውጥ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.11 | ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመቅረፍ በሚያደርጉት ጥረት መልካም ተሞክሮ ባላቸው ክልሎች በየአመቱ የልምድ ልውውጥ ሊደረግና ሊገመገም ይገባል ይገባል፡፡ |
| | 2.12 | የሴቶች የኢኮኖሚ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን የሚያመላክት ብሮሸሮች በየወቅቱ ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ |
| | 2.13 | የተዘጋጁትም ብሮሸሮች ለሚመለከታቸው ሊሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 2.14 | በደል ለደረሰባቸው ሴቶች የምክርና የሙያ አገልግሎት የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| 2. በሴቶች ጉዳይ ዙሪያ የተሟላ የመረጃ ፍሰት ስርዓት መኖሩን ማረጋገጥ | 3.1 | በአገሪቱ ውስጥ በስርዓተ ፆታ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች ሊሰበሰቡና በመረጃነት የሚያዙበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 3.2 | ስርዓተ ፆታን የተመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 3.3 | ሥርዓተ ፆታን ሜይንስትሪሚንግ ያደረጉ መ/ቤቶችና ድርጅቶች በሴቶች ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ በየሩብ አመቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ሊያደርጉ ይገባል፡፡ |
| | 3.4 | በመስክ የተገኙ መረጃዎችና ከአስፈፃሚ አካላት የሚሰበሰቡ ወቅታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶች መጠናቀር አለባቸው፡፡ |
| | 3.5 | የተጠናቀሩት ሪፖርቶች ሊተነተኑና እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል፡፡ |
| | 3.6 | ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስርዓተ ፆታን የሚመለከቱ መረጃዎችን በመረጃ መረብ ሊያሰራጭ ይገባል፡፡ |
| | 3.7 | የመረጃ መረቡም ቢያንስ በየሁለት ቀኑ ወቅታዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 3.8 | የስርዓተ ፆታ ጉዳይ ላይ በሚሰሩ አካላት መካከል የመረጃ ልውውጥ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |